# መጽሐፈ አስቴር

## መግቢያ

### ጸሐፊውና የተጻፈበት ጊዜ

ምንም እንኳ የመጽሐፈ አስቴር ጸሐፊ ማን እንደ ሆነ በውል ለማወቅ ባንችልም፣ ከመጽሐፉ ውስጣዊ ማስረጃዎች በመነሣት ጸሐፊው ማን እንደ ሆነና የተጻፈውም መቼ እንደ ሆነ መናገር ይቻላል። በአይሁድ በዓላት ላይ የተሰጠውን አጽንዖትና በትረካው ውስጥ የአይሁድ ብሔራዊ ስሜት ጎኖ ስናስተውል ጸሐፊው በእርግጥ አይሁድ መሆኑን እንገነዘባለን። በሌላ በኩል ደግሞ ጸሐፊው ስለ ፋርስ ሰዎች ባህል ያለውን ዕውቀት፣ የታሪኩ መቼት የሱሳ ከተማ መሆኗንና በታሪኩ ውስጥ ስለ ይሁዳ ወይም ስለ ኢየሩሳሌም ምድር ምንም አለመጠቀሱን ስንመለከት ጸሐፊው የፋርስ ከተማ ነዋሪ መሆኑን እንረዳለን። መጽሐፉ የተጻፈው ሁነቶቹ ከተፈጸሙ ከጥቂት ዓመታት በኋላ ማለትም በ460 ዓ.ቅ.ክ. ገደማ ነው (ይህም ዕዝራ ወደ ኢየሩሳሌም ከመመለሱ በፊት መሆኑ ነው፤ የ8፥12 ማብ ይመ)። ከዚህ በተጨማሪ ውስጣዊ ማስረጃዎች እንደሚጠቁሙት ይህ መጽሐፍ ከመጻፉ ጥቂት ቀደም ብሎ የፑሪም በዓል ይከበር ነበር (9፥19)። በርካታ ሊቃውንት እንደሚናገሩት ይህ መጽሐፍ የተጻፈው በግሪኮች ዘመን ነው፤ በመጽሐፉ ውስጥ የግሪክ ቃል ተጠቅሶ አለመገኘቱና ጸሐፊውም የዕብራይስጡን የቋንቋ ዘዬ ተከትሎ መጻፉ የሚያስረዳን ይህ መጽሐፍ የተጻፈው የፋርስ ግዛተ አፄ በ331 ዓ.ቅ.ክ. ላይ በግሪኮች እጅ ከመውደቁ በፊት ነው።

### ዓላማው፣መሪ ሐሳቡና ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ

የጸሐፊው ዋና ዓላማ የፑሪምን ዓመታዊ በዓል አከባበር በሚገባ መዘገብና መጪው ትውልድም በጠረክሲስ ዘመነ መንግሥት የተፈጸመውን ታላቁን ትድግና ሕያው በሆነ መንገድ እንዲያስታውሰው መርዳት ነው። መጽሐፉ የበዓሉን አከባበር ሥርዐትና በዓሉም ያለማቋረጥ በየዓመቱ መከበር እንዳለበት አጽንዖት ሰጥቶ ይተርካል (3፥7፤9፥24፡28-32፤ እንዲሁም በገጽ 178 ላይ "የብሉይ ኪዳን በዓላትና የተቀደሱ ቀናት" የሚለውን ይመ)። አብዛኛው የታሪኩ ክፍል የሚያተኵረው በእስራኤልና በአማሌቃውያን መካከል በነበረው ግጭት ላይ ነው (የ2፥5፤3፥1-6፤9፥5-10 ማብ ይመ)፤ ይህ ግጭት የጀመረው እስራኤላውያን ገና ከግብፅ በወጡ ማግስት ሲሆን (ዘፀ17፥8-16፤ዘዳ25፥17-19)፣ በታሪካቸው ሁሉ ያልተለዩ ጠላቶች ናቸው (1ሳሙ15፤1ዜና4፥43፤ እንዲሁም መጽሐፈ አስቴር በሙሉ)። እስራኤላውያን ከግብፅ ባርነት ነጻ እንደ ወጡ በመጀመሪያ ጠላት ሆነው የተነሡባቸው አማሌቃውያን ናቸው። እንግዲህ አማሌቃውያን የሚታዩት (የመጽሐፈ አስቴር ጸሐፊም የሚያያቸው) በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የተነሡ የክፉ ኀይሎች ምሳሌ ተደርገው ነው (ዘኍ24፥20፤1ሳሙ 15፥1-3፤ 28፥18 ይመ)። እስራኤል አሁን ነጻ ወጥታለች፤ የሐማም ዐዋጅ የእስራኤልን ሕዝብ ከምድረ ገጽ ለማጥፋት የተጠነሰሰ የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን ሤራ ነው።

ከአማሌቃውያን ግጭት ጋር ተዛምዶ የምናገኘው ለእግዚአብሔር ሕዝብ ተስፋ የተሰጠው ዕረፍት ነው (ዘዳ25፥19 ይመ)። ሐማ ድል ከሆነ በኋላ አይሁድ ከጠላቶቻቸው ሤራ ዕረፍት አገኙ (9፥16፡22)።

ጸሐፊው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ዘልቀው የምናገኛቸውን ጭብጦች (መቅሠፍት፣ በሽታ፣ ጦርነት፣ መዐት ወይም በዚህ ሁሉ ውስጥ አልፈው የሚተርፉትን ቅሬታዎች) በመጥቀስ ታሪኩን ይዘግባል። የፋርስ ከተማ በሆነችው በሱሳ የተፈጸሙት ሁነቶች የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ ለማደናቀፍ ሞክረው ነበር። የእግዚአብሔር ሕዝብ ህልውና በተለይም የቤዛዊ መሲሑ መገለጥ፣ ሐማ አይሁድን ለማጥፋት ባወጣው ዐዋጅ አደጋ ላይ ሲወድቅ ይታያል። የመጽሐፈ አስቴር ጸሐፊ ታሪኩን የቀረጸው በዮሴፍ ታሪክ አምሳያ ነው (የ2፥3-4፡9፡21-23፤3፥4፤4፥14፤ 6፥1፡8፡14፤8፥6 ማብ ይመ)፤ በዚህ ትረካ ውስጥ ትልቁን ስፍራ የያዘው የቅሬታዎች ጭብጥ ነው (ዘፍ 45፥7)። ከዚህ በታች ከቀረበው አስተዋፅኦ ማስተዋል እንደሚቻለው፣ ክብረ በዓል በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ ዐቢይ ስፍራ አለው። በየጊዜው የተደረጉት ግብዣዎች ለትረካው ውቅር (የታሪክ መዋቅር) ዋና መድረክ ናቸው። በዚህ ትረካ ውስጥ ዐሥር ግብዣዎች ተጠቅሰዋል (1)1፥3-4፣ (2)1፥5-8፣ (3)1፥9፣ (4)2፥18፣ (5)3፥15፣(6)5፥1-8፣ (7)7፥1-10፣ (8)8፥17 (9)9፥17፣ (10)9፥18-32። ሦስቱ ጥንድ ግብዣዎች ማለትም በትረካው መጀመሪያ፣ መካከልና መጨረሻ ላይ የሚገኙት ግብዣዎች የላቀ ስፍራ አላቸው፤ እነዚህም በአርጤክስስ የተደረጉት ሁለት ግብዣዎች፣ አስቴር ያዘጋጀችው ሁለት ግብዣዎችና ዕጥፍ ድርብ በዓል ሆኖ የተከበረው የፑሪም በዓል ናቸው።

ጸሐፊው ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ታሪኮች መልሶ መላልሶ በመዘገብ የተለየ ያጻጻፍ ዘዬ ተከትሏል። ጥንድ ጥንድ ሆነው ከተጠቀሱት ከሦስቱ ግብዣዎች ሌላ፣ ሁለት የንጉሡ አገልጋዮች ስም ዝርዝር (1፥10፡14)፣ ሁለት ጊዜ አስቴር ማንነትዋን መደበቋ (2፥10፡20)፣ ሁለት ጊዜ ሴቶች መሰብሰባቸው (2፥8፡19)፣ ሁለት የሴቶች ቤት (2፥12-14)፣ ሁለት ጾሞች (4፥3፡16)፣ ሐማ ከሚስቱና ከወዳጆቹ ጋር ያደረጋቸው ሁለት ምክሮች (5፥14፤6፥13)፣ አስቴር ሁለት ጊዜ ቀጠሮ ሳትይዝ ወደ ንጉሡ መግባቷ (5፥2፤8፥3)፣ መርዶክዮስ ሁለት ጊዜ የክብር ልብስ ለብሶ መታየቱ (6፥7-11፤8፥15)፣ ሐማ ፊቱን ሁለት ጊዜ መሸፈኑ (6፥12፤7፥8)፣ ሁለት የሐማ ወንዶች ልጆች (5፥11፤9፥6-10፡13-14)፣ ሐርቦና ሁለት ጊዜ በንጉሡ ፊት መቅረቡ (1፥10፤7፥9)፣ ሁለት የንጉሡ ዐዋጆች (3፥12-14፤8፥1-13)፣ የንጉሡ ቍጣ

ሁለት ጊዜ መብረዱ (2፥1፤7፥10)፣ የፋርሶች ሕግ እንደማይሻር ሁለት ጊዜ መጠቀሱ (1፥19፤8፥8)፣ አይሁድ ሁለት ቀን ጠላቶቻቸውን መበቀላቸውና (9፥5-15)፣ የፑሪም በዓል በመታሰቢያነት እንዲከበሩ የሚያሳስቡ ሁለት ደብዳቤዎች (9፥20-32) ናቸው።

ይህን መጽሐፍ ልዩ ከሚያደርጉት ባሕርያት ውስጥ ጥቂቶቹ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ አምልኮ፣ ስለ ጸሎትና ስለ መሥዋዕት አንድም ጊዜ አለመወሳቱ ነው። ይህም በብዙ ሊቃውንት ዘንድ ጥያቄ አስነሥቷል። ጥያቄውም መጽሐፉ መንፈሳዊ ፋይዳ አለው ወይ? የሚለው ነው። የእግዚአብሔር "ስሙ" እንኳ ያልተጠቀሰበት መጽሐፍ ምን መንፈሳዊ ረብ አለው? ጸሓፊው ግን እንዲህ ያደረገው ሆን ብሎ ነው። የእግዚአብሔርን ስም ሆን መንፈሳዊና ሃይማኖታዊ ሥርዐቶችን ያልጠቀሰው ሰዎች ከቁብ የማይቈጥሯቸውን አጋጣሚዎች የሚመራና የሚቈጣጠር እግዚአብሔር መሆኑን በተለየ የአጻጻፍ ስልት ለመግለጽ ነው (የ6፥1 ማብ ይመ)። ትረካውና የእስራኤል ትድግና የተመሠረተው ጸሓፊው ሆን ብሎ በዝምታ ባለፋቸው ነገሮች ላይ ነው። እግዚአብሔር ልዑልና ገዥ እንደ ሆነ የምናየው በቀጥታ ሳይሆን በተዘዋዋሪ ነው (የ4፥12-16 ማብ ይመ)፤ ስሙ ባይጠቀስም ሥራው ግን ሕያው ሆኖ በግልጽ ይታያል።

**አስተዋፅኦ**

1. የአርጤክስስ ግብዣ(1፥1-2፥18)
   ሀ. ንግሥት አስጢን ከዙፋኗ ወረደች (ም1)
   ለ. አስቴር ንግሥት ሆነች (2፥1-18)
2. የአስቴር ግብዣ (2፥19-7፥10)
   ሀ. መርዶክዮስ ሤራውን ደረሰበት (2፥19-23)
   ለ. የሐማ ሤራ (ም3)
   ሐ. አስቴር ርዳታ እንድታደርግ መርዶክዮስ ያቀረበው ማሳሰቢያ (ም4)
   መ. አስቴር ለንጉሡ ያቀረበችው ጥያቄ፤ የመጀመሪያው ግብዣ (5፥1-8)
   ሠ. እንቅልፍ ከንጉሡ የሸሸበት ሌሊት (5፥9-6፥14)
   ረ. ሐማ ተሰቀለ፤ ሁለተኛው ግብዣ (ም7)
3. የፑሪም በዓል (ም8-10)
   ሀ. ንጉሡ በአይሁድ ስም ያስተላለፈው ዐዋጅ (ም8)
   ለ. የፑሪም በዓል አከባበር (ም9)
   ሐ. መርዶክዮስ የላቀ ሹመት ማግኘቱ (ም10)

## ንግሥት አስጢን ከክብሯ ወረደች

**1** ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮጵያ ድረስ
ያሉትን አንድ መቶ ሃያ ሰባት አገሮች
ይገዛ በነበረው በአርጤክስስ ዘመን መንግ
ሥት እንዲህ ሆነ፤ 2በዚያን ዘመን ንጉሡ
አርጤክስስ የገዛው በሱሳ ግንብ ባለው ን
ጉሣዊ ዙፋኑ ሆኖ ነበር። 3እርሱም በነገሠ
በሦስተኛው ዓመት ለመኳንንቱና ለሹማ
ምቱ ሁሉ ታላቅ ግብዣ አደረገ። በግብ
ዣውም የፋርስና የሜዶን የጦር አዛዦች፣
መሳፍንትና የየአውራጃው መኳንንት ተገኝ
ተው ነበር።
4ለእነርሱም የመንግሥቱን ሰፊ ሀብት፣
የግርማውን ታላቅነትና ክብር አንድ መቶ
ሰማንያ ቀን ሙሉ አሳያቸው። 5እነዚህ
ቀናት ካለፉ በኋላ፣ ንጉሡ በሱሳ ግንብ
ለነበሩት፣ ከትንሽ እስከ ትልቅ ላለው ሕ
ዝብ ሁሉ፣ በቤተ መንግሥቱ ውስጥ
ዙሪያውን በአትክልት በተከበበው አደባባይ
ሰባት ቀን የፈጀ ግብዣ አደረገ። 6አደባባ
ዩም ከነጭና ከሰማያዊ በፍታ የተሠሩ መጋ
ረጃዎች ነበሩት፤ እነርሱም የብር ቀለበት
በተበጀላቸው፣ ከነጭ በፍታና ከሐምራዊ
ቀለም በተሠሩ ገመዶች በዕብነ በረዱ ምሰ
ሶዎች ላይ ተንጠልጥለው ነበር። ነጭና ቀይ
ቀለማት ተሰበጣጥረው በተነጠፉበት ወለል
ላይ የወርቅና የብር ድንክ ዐልጋዎች ነበሩ፤
እነርሱም ከዕብነ በረድ፣ ቀስተ ደመና
ከሚመስሉ ቀለሞችና ከሌሎች የከበሩ
ድንጋዮች የተሠሩ ነበሩ። 7የወይን ጠጅም
አንዱ ከሌላው ልዩ በሆነ የወርቅ ዋንጫ
ይቀርብ ነበር፤ ከንጉሡም ልግስና የተነሣ
የቤተ መንግሥቱ የወይን ጠጅ የተትረፈ
ረፈ ነበር። 8ንጉሡ ለእያንዳንዱ ሰው የሚ
ፈልገውን ያህል እንዲያቀርቡለት የወይን
ጠጅ አሳላፊዎቹን ሁሉ አዝዞ ስለ ነበረ፣ በን
ጉሡ ትእዛዝ መሠረት እያንዳንዱ ተስተና
ጋጅ እንዲጠጣ ተፈቅዶለት ነበር።
9ንግሥት አስጢንም በንጉሥ አርጤክስስ
ቤተ መንግሥት እንደዚሁ ለሴቶች ግብዣ
አድርጋ ነበር።
10በሰባተኛው ቀን ንጉሥ አርጤክስስ ከወ
ይን ጠጁ የተነሣ ደስ ስለ ተሰኘ፣ አገልጋ
ዮቹ የሆኑትን ሰባቱን ጃንደረቦች ምሁማ
ንን፣ ባዛንን፣ ሐርቦናን፣ ገበታን፣ ዘቶልያ
ንን፣ ዜታርንና ከርከስን እንዲህ ብሎ አዘዛ
ቸው፤ 11ይኸውም ንግሥት አስጢን የደስ
ደስ ያላት ነበረችና ውበቷ ለሕዝቡና
ለመኳንንቱ እንዲታይ ዘውዷን ጭና ንጉሡ
ፊት እንዲያመጧት ነበር። 12አገልጋዮቹ
የንጉሡን ትእዛዝ በነገሯት ጊዜ ግን፣ ንግ
ሥት አስጢን መሄድ አልፈለገችም። ከዚያም
ንጉሡ በጣም ተቈጣ፤ እጅግም ተናደደ።
13ሕግንና ፍትሕን በተመለከተ የሊቃውን
ቱን ምክር መጠየቅ በንጉሥ ዘንድ የተለ
መደ ነበርና፣ ስለ ዘመናት ሁኔታ ዕውቀት
ካላቸው ጠቢባን ጋር ተነጋገረበት፤ 14እነዚህ
አርቄስዮስ፣ ሺታር፣ አድማታ፣ ተርሺሽ፣
ሜሬስ፣ ማሌሴዓር፣ ምሙካ የተባሉ ሰባቱ
የፋርስና የሜዶን መኳንንት በንጉሡ ዘንድ
የተለየ ስፍራና በመንግሥቱም አመራር
ውስጥ ከፍተኛ ቦታ ያላቸው ነበሩ።
15ንጉሡም፣ "በጃንደረቦቹ በኩል የተ
ላከባትን የንጉሥ አርጤክስስን ትእዛዝ ስላ
ልፈጸመች፣ በሕጉ መሠረት በንግሥት አስ
ጢን ላይ ምን መደረግ አለበት?" ሲል ጠየ
ቃቸው።
16ከዚያም ምሙካ በንጉሡና በመኳንንቱ
ፊት እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ንግሥት አስ
ጢን የበደለችው ንጉሡን ብቻ ሳይሆን፣

1፥1 ዕዝ4፥6፤አስ 8፥9፤9፥30፤ዳን3፥2፤ 6፥1
1፥2 ዕዝ4፥9፤ አስ2፥8
1፥3 1ነገ3፥15
1፥5 መሳ14፥17፤ 2ነገ21፥18
1፥6 አስ7፥8፤ሕዝ 23፥41፤አሞ3፥12፤ 6፥4
1፥7 አስ2፥18፤ ዳን5፥2
1፥9 1ነገ3፥15
1፥10 ዘፍ14፥18፤ መሳ16፥25፤ሩት 3፥7፤አስ3፥15፤5፥6፤7 ፥2፤ምሳ31፥4-7፤ ዳን5፥1-4
1፥11 መዝ45፥11፤ መሓ2፥4፤ሕዝ16፥14
1፥12 ዘፍ39፥19፤ አስ2፥21፤7፥7፤ምሳ19 ፥12
1፥13 1ዜና12፥32
1፥14 አስ7፥14

1፥1 *አርጤክስስ፤* የዕዝ 4፥6 ማብ ይመ። አርጤክስስ በአባቱ በዳርዮስ ምትክ ነግሦ፣ ከ486-465 ዓ.ቅ.ክ በፊት የገዛ ንጉሥ ነበር። *መቶ ሃያ ሰባት አገሮች፤* 8፥9 ይመ። እዚህ ላይ 'አገሮች' የተባሉት መለስተኛ አውራጃዎች የነበሩ ናቸው። የአርጤክስስ አባት ንጉሥ ዳርዮስ ግዛቱን በሃያ ክፍላተ አገር በመከፋፈል ለእያንዳንዱ አስተዳዳሪ መድቦ እንደ ነበር፣ ግሪካዊው ታሪክ ጸሐፊ ሄሮዱቱስ ጠቅሶ ጽፎአል።

1፥2 *በሱሳ ግንብ፤* በምሽግ መልክ ከፍ ብሎ የተሠራ የቤተ መንግሥቱ ሕንጻ አካል ነበር፤ በአካባቢው ካለው ከተማ የተለየ መሆኑ በ3፥15፤ 4፥1-2፡6፤8፥15 ላይ ተገልጾአል። ከዐሥራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ በአካባቢው ብዙ የሥነ ቅርስ ቍፋሮ ምርምር ተካሂዶአል። አርጤክስስ የቤተ መንግሥቱን ሕንጻ ሥራ ለማስዋብ ብዙ የእድሳት ሥራ አከናውኖአል። *ሱሳ፤* የፋርስ ነገሥታት በክረምት የሚያርፉባት ከተማ ነበረች፤ ሌሎቹ የፋርስ ዋና ዋና ከተሞች አሕምታ (ዕዝ 6፥2)፣ ባቢሎንና ጳርሰጶሊስ የተባሉት ነበሩ። ዳንኤል ከራእዮቹ በአንዱ ሱሳን ተመልክቶአል (ዳን 8፥2)፤ ነህምያ በዚች ከተማ አገልግሎአል (ነህ 1፥1)።

*1፥3-4፤* በሦስተኛው ዓመት (483-482 ዓ.ቅ.ክ በፊት)፣ በዚያ የተገኙት ሰዎችና የስብሰባው የጊዜ ርዝመት፣ ምናልባት ጉባኤው የተካሄደው በ482-479 ዓ.ቅ.ክ በግሪክ ላይ አደገኛ ዘመቻ ለማቀነባበር ሳይሆን እንደማይቀር ያመለክታል። ሄሮዱቱስ የተባለው ግሪካዊ የታሪክ ጸሐፊም (በመጽሐፉ ምን ቍ 8 ላይ) የገለጸው ስብሰባ ይህ ሳይሆን አይቀርም።

1፥3 *ግብዣን* በአስቴር መጽሐፍ ውስጥ ግብዣ ጐላ ብሎ የሚታይ መሪ ሐሳብ ነው።

*1፥5-6፤* በቍፋሮ ከተገኘው የሱሳ ፍርስራሽ ውስጥ የአርጤክስስ አባት ንጉሥ ዳርዮስ ስለ ቤተ መንግሥቱ ሕንጻ ሥራ በዝርዝር የጻፈው ጽሑፍ ተገኝቶአል። አርጤክስስ አባቱ ጀምሮት የነበረውን ሥራ ቀጠለ።

1፥9 *ንግሥት አስጢንም፤* ከእቴጌነቷ በ484/483 ዓ.ቅ.ክ እንድትወርድ ተደርጋለች፤ አስቴር በ489/478 ዓ.ቅ.ክ ንግሥት ሆናለች (2፥16-17)። ግሪካውያን የታሪክ ጸሐፊዎች የንጉሥ ጠረክሲስን ንግሥት 'አሜስጥሪስ' ይሏታል፤ በንጉሡ ነገሥቱ የግዛት ዘመን መጀመሪያ ላይ፣ ልጇ አርጠዘሬክስስ ከነገሠ በኋላ እናቱ እቴጌ በመሆን እስከ ዕለተ ሞቷ ድረስ (424 ዓ.ቅ.ክ) በመንግሥት ተግባር ስለ ተጫወተችው ሚናና ስላሳደረችው ወሳኝ ተጽዕኖ ጽፈዋል (ስለ አርጠዘሬክስስ ዕዝ7፥1፡7፡11-12፡21፤8፥1፤ነህ2፥1፤5፥14፤13፥6 ይመ)፤ አርጠዘሬክስስ የነገሠው ገና የዐሥራ ስምንት ዓመት ወጣት ሳለ በመሆኑ የተወለደው በ484/483 ዓ.ቅ.ክ ገደማ ነው ማለት ይቻላል፤ ይህም ንግሥቲቱ አስጢን ከሥልጣን የወረደችበት ዓመት አካባቢ ነው። አርጠዘሬክስስ የንግሥት አሜስጥሪስ ሦስተኛ ልጅ መሆኑ ይታወቃል፤ ስለዚህ 'አሜስጥሪስ' የሚለው ስም የንግሥት አስቴር ስም ነው ለማለት ያዳግታል፤ በመሆኑም ግሪኮች ለንግሥት አስጢን የሰጧት ሌላ ስም ነው ለማለት እንገደዳለን። ከሌሎች ነገሥታት ሁኔታ አንጻር ስንመለከት፣ ስለ ንጉሥ አርጤክስስ የመጨረሻ ዕድል ፈንታ የሚታወቅ ነገር እንዳለ መግለጥ አይቻልም፤ የንግሥት አስቴር የመጨረሻ ሁኔታም ምን ይመስል እንደ ነበረ ማወቅ አስቸጋሪ ነው። አስቴር ከሞተች በኋላ ወይም ጊዜ ከጣላት በኋላ፣ ንግሥት አስጢን እንደ ገና ሥልጣን አግኝታ ልጇን በፈለገችው አቅጣጫ ለመምራት ችላ ነበር ማለት ይቻላል።

*1፥13-14፤* ዕዝ 7፥14 ላይ እንደ ተጠቀሰውና ግሪካዊው ታሪክ ጸሐፊ ሄሮዱቱስ እንደ ጻፈው፣ ንጉሡ ሰባት የቅርብ አማካሪዎች ነበሩት።

1፥13 *ስለ ዘመናት ሁኔታ ዕውቀት ካላቸው፤* በቤተ መንግሥቱ ውስጥ የሚያገለግሉ ኮከብ ቈጣሪዎች ናቸው።

መኳንንቱን ሁሉና በመላው የንጉሥ አርጤ
ክስስ አውራጃዎች የሚኖሩትን ሕዝቦች
ጭምር ነው:: 17ይህ የንግሥቲቱ አድራጎት
በሌሎቹ ሁሉ ዘንድ ስለሚሰማ፣ ባሎቻቸ
ውን ይንቃሉ፤ ‘ንጉሥ አርጤክስስ ንግሥት
አስጢን ወደ እርሱ እንድትመጣ ቢያዛትም፣
እርሷ ግን መሄድ አልፈለገችም’ ይላሉ::
18በዚህች በዛሬዪቱም ዕለት የንግሥቲቱን
አድራጎት የሰሙ የፋርስና የሜዶን መኳን
ንት ሚስቶች፣ ለንጉሡ መኳንንት ሁሉ
በዚሁ ዐይነት ሊመልሱ ነው፤ እንዲህ ከሆነ
ደግሞ ማብቂያ የሌለው ንቀትና ጠብ
ይፈጠራል::

19“ስለዚህ ነገሩ ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው
ከሆነ፣ አስጢን ወደ ንጉሡ ወደ አርጤክ
ስስ ዘንድ ከእንግዲህ ወዲህ ፈጽሞ እንዳ
ትገባ ንጉሣዊ ዐዋጅ ይውጣ፤ ይህም የማይ
ሻር ሆኖ በፋርስና በሜዶን ሕጎች ይጻፍ፤
እንዲሁም ንጉሡ የእቴጌነቷን ክብር ከእ
ርሷ ለምትሻል ለሌላዪቱ ይስጥ:: 20ከዚያም
የንጉሡ ዐዋጅ በሰፊው ግዛቱ ሁሉ ሲነገር፣
ከትንሽ እስከ ትልቅ ያሉት ሴቶች ሁሉ
ባሎቻቸውን ያከብራሉ::”

21ንጉሡና መኳንንቱ ሁሉ በዚህ ምክር
ተደሰቱ፤ ንጉሡም ምሙካ ያቀረበውን ሐሳብ
በሥራ ላይ አዋለው:: 22እያንዳንዱ ሰው በራሱ
ቤተ ሰብ ላይ ገዥ እንዲሆን መልእክት
አስተላለፈ፤ መልእክቱም ለየአውራጃዎቹ
በየራሳቸው ጽሑፍና ለእያንዳንዱ ሕዝብ
በየራሱ ቋንቋ ተጽፎ በግዛቱ ሁሉ ተበተነ::

1፥18 ምሳ19፥13፤ 27፥15
1፥19 አስ8፥8፤መክ 8፥4፤ዳን6፥8:12
1፥22 ነህ13፥24
2፥1 አስ7፥10
2፥5 1ሳሙ9፥1
2፥6 2ነገ24፥15፤ ዳን1፥1-5፤5፥13
2፥7 ዘፍ39፥6፤ 41፥45

## አስቴር ንግሥት ሆነች

2ከዚህ በኋላ ንጉሡ አርጤክስስ ቍጣው
ሲበርድለት አስጢንን፣ ያደረገችውን
ነገርና በእርሷም ላይ ያስተላለፈውን ዐዋጅ
ዐሰበ:: 2ከዚያም የንጉሡ የቅርብ አገልጋዮች
እንዲህ የሚል ሐሳብ አቀረቡ፤ “ለንጉሡ
ቈንጆ ልጃገረዶች ይፈለጉለት፤ 3እነዚህን
ሁሉ ቈንጆ ልጃገረዶች በሱሳ ግንብ ወደ
ሚገኘው ልዩ የሴቶች መኖሪያ ቦታ እንዲ
ያመጡ፣ ንጉሡ በግዛቱ በሚገኙት አውራ
ጃዎቹ ሁሉ ባለሥልጣኖችን ይሹም፤ እነር
ሱም የሴቶች የበላይ ኀላፊ በሆነው በንጉሡ
ጃንደረባ በሄጌ ኀላፊነት ሥር ይሁኑ፤ የው
በትም እንክብካቤ ይደረግላቸው:: 4ከዚያም
ንጉሡን ደስ የምታሰኘው ልጃገረድ በአስጢን
ፈንታ ንግሥት ትሁን::” ምክሩ ንጉሡን ደስ
አሰኘው፤ በተባለውም መሠረት አደረገ::

5በዚህ ጊዜ ከብንያም ነገድ የቂስ ልጅ፣
የሰሜኢ ልጅ፣ የኢያዕር ልጅ መርዶክዮስ
የሚባል አንድ አይሁዳዊ በሱሳ ግንብ ይኖር
ነበር፤ 6እርሱም የባቢሎን ንጉሥ ናቡከደነፆር
ከማረካቸው ከይሁዳ ንጉሥ ከኢኮንያን[ሀ] ጋር
ከኢየሩሳሌም በምርኮ ከተወሰዱት አንዱ ነበር::
7መርዶክዮስ አንዲት ሀደሳ የምትባል የአጎቱ
ልጅ ነበረችው፤ አባትና እናት ስላልነበራት፣
ያሳደጋት እርሱ ነበር:: አስቴር ተብላ የም

ሀ6 በዕብራይስጥ፣ *ኢኮንያን* የሚለው ስም *ኢዮአቄም* ከሚለው ጋር አንድ ዐይነት ነው::

1፥19 ***የማይሻር፤*** የፋርስ ሕግ አንድ ጊዜ ከወጣ፣ ፈጽሞ የማይለወጥ ስለ መሆኑ 8፥8 ላይ እንዲሁም ዳን 6፥8 ላይ ተጠቅሷል:: ***ከእንግዲህ ወዲህ ፈጽሞ እንዳትገባ፤*** አስጢን ንጉሡ ፊት አልቀርብም ስላለች፣ ዳግመኛ ንጉሡ ፊት እንዳትቀርብ የሚል ከሠራችው ወንጀል ጋር የሚመጣጠን ቅጣት ተወሰነባት፤ ከዚህም በተጨማሪ፣ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ ‘ንግሥት’ የሚለው ማዕረግ ተነፍጓታል::

1፥22 ***ቤተ ሰብ ... መልእክት፤*** ይህ ሐረግ፣ “እያንዳንዱ ወንድ የቤተ ሰቡ አስተዳዳሪ መሆንና በቤቱም ውስጥ የራሱ ቋንቋ መነገር አለበት” ሊባል ይችላል፤ ይህም ከተለያየ ወገን በተጋቡ ቤተ ሰብ ውስጥ የወንዱ ቋንቋ መነጋገሪያ መሆን በቤተ ሰቡ ላይ የባልዩውን የበላይነት ያመለክታል (ነህ13፥23-24 ይመ)::

2፥1 ***በኋላ፤*** አስቴር ወደ ንጉሡ የተወሰደችው፣ ንጉሡ “በነገሠ በሰባተኛው ዓመት” ነበር (ቍ 16)፤ ይኸውም በታህሣሥ ወር 479 ዓ.ቅ.ክ ወይም በጥር ወር 478 ዓ.ቅ.ክ መሆኑ ነው:: ከግሪኮች ጋር የነበራቸው ጦርነት አዲስ ንግሥት የመሾሙን ጒዳይ ሳያዘገየው እንዳልቀረ ይገመታል (የ1፥3-4 ማብ ይመ)::

2፥2 ***ለንጉሡ ... ልጃገረዶች፤*** ቀደም ሲል በነበሩት ቅምጦቹ ላይ ለመጨመር ነው::

*2፥3-4፤* እዚህ ላይ የሚገኘው የሐረጎች አገባብ በዘፍ 41፥34-37 ላይ ካለው አገላለጽ ጋር ተመሳሳይነት አለው:: ይህና ሌሎችም በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የሚገኙ ተመሳሳይ የአባባል ዘይቤዎች መጽሐፈ አስቴርን የጻፈው ሰው የዮሴፍን ታሪክ አጻጻፍ እንደ መመሪያ የተጠቀመበት መሆኑን ያመለክታሉ:: ሁለቱም ታሪኮች በባዕድ አገር ነገሥታት አደባባዮች የተከናወኑ ሲሆኑ፣ በሁለቱም ውስጥ ለሕዝባቸው መዳን ሁኔታዎችን ያመቻቹና ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ የእስራኤል ጀግኖች ታሪክ ተገልጦአል (የቍ 9:21-23፤ 3፥4፤ 4፥14፤ 6፥1:8:14፤ 8፥6 ማብ ይመ)::

2፥5 ***አንድ አይሁዳዊ በሱሳ ግንብ፤*** የሰሜኑ መንግሥት በ722-721 ዓ.ቅ.ክ ከወደቀ በኋላ፣ እስራኤላውያን በሜዶን ከተሞች ምርኮኛ ሆነው ኖረዋል (2ነገ 17፥6):: የባቢሎን ንጉሥ በ539 ዓ.ቅ.ክ በፋርሱ ንጉሥ ቂሮስ ከተመታ በኋላ፣ ጥቂት አይሁዳውያን ወደ ምሥራቅ ሜዶፋርስ ከተሞች በባቢሎናውያን አማካይነት (በ605-586 ዓ.ቅ.ክ) ሳይፈልሱ አልቀሩም:: በ583 ዓ.ቅ.ክ ከምርኮ የተመለሱት 50000 ሰዎች ብቻ ነበሩ (ዕዝ 2፥64-67):: “ኒፑር” በተባለው ስፍራ (ደቡብ መስጴጦምያ) በንጉሥ አርጤ*ዘረክስስ ቀዳማዊና* (465-424 ዓ.ቅ.ክ)በዳርዮስ *ዳግማዊ* (424-405 ዓ.ቅ.ክ) ዘመን የተገኘው የታሪክ ስፍራ ሰነድ ከፍተኛ ቍጥር ያለው የአይሁድ ሕዝብ በሜዶፋርስ ይኖር እንደ ነበር ይጠቁማል:: በዚህ ሰነድ ውስጥ፣ በዚያ ከተማ ይኖሩ የነበሩ፣ ቢያንስ የአንድ መቶ አይሁድ ስሞች ተገኝተዋል:: ከእነርሱም አንዳንዶቹ የክብር ስፍራ የነበራቸው ናቸው:: በሌሎችም የሜዶ-ፋርስ ከተሞች ይህንኑ ያህል ቍጥር ያላቸው የአይሁድ ዜጎች ይኖሩ እንደ ነበር ይገመታል:: ***መርዶክዮስ፤*** ስሙ “ማርዱክ” ከተባለው የባቢሎናውያን ባዕድ አምላክ ጋር የተያያዘ ነው:: የአይሁድ ሕዝብ አንድ የዕብራውያን፣ አንድ የ“አሕዛብ” ስም እንደ ነበራቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ብዙ ምሳሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፤ እንደ አስቴር ሁሉ (ቍ 7) መርዶክዮስም ዕብራዊ ስም እንደ ነበረው መገመት ይቻላል፤ ዳንኤልና ባልንጀሮቹ (ዳን 1፥6-7)፣ ዮሴፍና (ዘፍ 41፥45) ሌሎችም ዕብራዊ ስም ነበራቸው:: ሆኖም የመርዶክዮስ ዕብራዊ ስም በዚህ መጽሐፍ አልተጠቀሰም:: በባቢሎን ከተማ አቅራቢያ፣ ቦርሲጳ በተባለ ስፍራ የተገኘ ጽሑፍ መርዱካያ ስለ ተባለ አንድ ጸሓፊ ይናገራል፤ እርሱም በሱሳ ቤተ መንግሥት በንጉሥ አርጤክስስ ዘመን መጀመሪያ ላይ የገንዘብ ቤት ሹም ወይም ሚኒስቴር የነበረ ሰው ነው:: በርካታ የመጽሐፍ ቅዱስ ሊቃውንት ይህ ሰው በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ የምናገኘው መርዶክዮስ ነው ይላሉ:: ***የቂስ ልጅ፣ የሰሜኢ ልጅ፣ የኢያዕር ልጅ፤*** የመርዶክዮስ ቅድመ አያት ቂስ በ597 ዓ.ቅ.ክ ከኢዮአቄም ጋር ተማርኮ የሄደ ሰው ነበር:: ይሁን እንጂ እነዚህ ስሞች ከብንያም ነገድ የጥንት አባቶችን የሚያመለክቱ ይመስላሉ፡ (ሰሜኢ ለሚለው 2ሳሙ 16፥ 5-14፤ ቂስ ለሚለው ደግሞ 1ሳሙ 9፥1 ይመ):: ይህ ነገድ ከንጉሥ ሳኦል ቤተ ሰብ ጋር የነበረው ግንኙነት በእስራኤልና በአማሌቃውያን መካከል እየተካሄደ ለነበረው ግጭት መንገድ (የ3፥1-6 ማብ ይመ) ይከፍታል:: እነዚህ ስሞች የጥንት የነገድ አባቶች ስሞች ከሆኑ፣ “በምርኮ ከተወሰዱት አንዱ” (ቍ 6) የሚለው ሐረግ መርዶክዮስን የሚመለከት አይሆንም፤ ምክንያቱም የመርዶክዮስን ዕድሜ ከመቶ ዓመት በላይ ያደርገዋል:: ስለዚህ ከዚህ ይልቅ ትክክል የሚሆነው፣ “ቤተ ሰቡ በምርኮ ከተወሰደበት አንዱ” የሚለው ነው::

2፥6 ***ከይሁዳ ንጉሥ ከኢኮንያን፤*** 2ነገ 24፥8-17፤ 2ዜና 36፥9-10 ይመ::

2፥7 ***ሀደሳ*** የአስቴር የዕብራይስጥ ስም ሲሆን፣ ትርጒሙም “ባርሰነት” ማለት ነው:: አስቴር የሚለው ስም ከፋርስ ቋንቋ

ትጠራው ይህች ልጃገረድ በተክለ ሰውነቷም
ሆነ በመልኳ እጅግ ውብ ነበረች። አባቷና
እናቷ ከሞቱ በኋላ መርዶክዮስ እንደ ራሱ
ልጅ አድርጎ ወሰዳት።
[8]የንጉሡ ትእዛዝና ዐዋጅ በወጣ ጊዜ፣
ብዙ ልጃገረዶች ወደ ሱሳ ግንብ ተወስደው
ለጠባቂው ለሄጌ ተሰጡ፤ አስቴርም ወደ ንጉሡ
ቤተ መንግሥት ተወስዳ፣ ለሴቶቹ ጠባቂ
ለሄጌ በዐደራ ተሰጠች። [9]ልጃገረዲቱም ደስ
አሰኘችው፤ በእርሱም ዘንድ መወደድን አተ
ረፈች፤ እርሱም የውበት መንከባከቢያዋንና
የተለየ ምግብ ወዲያውኑ ሰጣት። ከቤተ
መንግሥቱ የተመረጡ ሰባት ደንገጡሮችን
በመመደብም እርሷንና ደንገጡሮቿን ምርጥ
ወደ ሆነው የሴቶች መጠበቂያ አዛወረ።
[10]መርዶክዮስ እንዳትናገር አዞአት ስለ
ነበር፣ አስቴር የየት አገር ሰውና የእነማን
ወገን እንደ ሆነች አልገለጸችም። [11]መርዶክ
ዮስም አስቴር እንዴት እንደ ሆነችና ምን
እንዳጋጠማት ለማወቅ፣ በየዕለቱ በሴቶች
መጠበቂያ አደባባይ አጠገብ ወዲያና ወዲህ
ይመላለስ ነበር።
[12]አንዲት ልጃገረድ ወደ ንጉሥ አርጤክስስ
ዘንድ ለመግባት ተራዋ ከመድረሱ በፊት
ስድስት ወር በከርቤ ዘይት፣ ስድስት ወር
ደግሞ ልዩ ልዩ ሽቱ በመቀባትና በተለያዩ
የፊት ቀለሞች በመዋብ ባጠቃላይ ዐሥራ
ሁለት ወር መቈየት ነበረባት፤ [13]ወደ ንጉሡ
ዘንድ የምትገባውም በዚህ ሁኔታ ሲሆን፣
ሴቶቹ ከሚኖሩበት ስፍራ ወደ ንጉሡ ቤተ
መንግሥት ስትሄድ፣ መውሰድ የምትፈልገው
ማናቸውም ነገር ይሰጣት ነበር። [14]ሲመሽ
ወደዚያው ትሄዳለች፤ ሲነጋም የቁባቶች
ኀላፊ በሆነው በንጉሡ ጃንደረባ በሻአሽጋዝ
ጥበቃ ሥር ወደሚገኘው ወደ ሌላው የሴ
ቶች መጠበቂያ ቤት ትመለሳለች፤ ደስ
የተሰኘባት ካልሆነችና በስሟም ካልጠራት
ዳግመኛ ወደ ንጉሡ ዘንድ አትገባም።
[15]መርዶክዮስ እንደ ልጁ አድርጎ ያሳደ
ጋት የአጎቱ የአቢካኢል ልጅ አስቴር ወደ
ንጉሡ ዘንድ የምትሄድበት ተራ በደረሰ ጊዜ
የሴቶች ልዩ ጥበቃ ቤት ኀላፊ የሆነው ሄጌ
የነገራትን እንጂ፣ ሌላ ምንም አልጠየቀችም።
አስቴር በሚያዩዋት ሁሉ ዘንድ ሞገስ አገ
ኘች። [16]በነገሠ በሰባተኛው ዓመት ቴቤት
በተባለው በዐሥረኛው ወር ወደ ንጉሥ
አርጤክስስ ቤተ መንግሥት ተወሰደች።
[17]በዚህ ጊዜ ንጉሡ ከሌሎቹ ሴቶች ሁሉ
ይበልጥ አስቴርን ወደዳት፤ ከሌሎቹ ደና
ግልም ሁሉ ይልቅ በእርሱ ዘንድ ሞገስንና
መወደድን አገኘች። ስለዚህ የእቴጌነት
ዘውድ በራሷ ላይ ጫነላት፤ በአስጢንም
ፈንታ ንግሥት አደረጋት። [18]ንጉሡም ስለ
አስቴር ክብር ለመኳንንቱና ለሹማምቱ
ሁሉ ታላቅ ግብዣ አደረገ፤ በዓሉም በየአ
ውራጃዎቹ ሁሉ እንዲከበር ዐወጀ፤ በንጉ
ሣዊ ልግስናውም ስጦታ አደረገ።

### መርዶክዮስ በንጉሡ ላይ የተጠነሰሰውን ሤራ ደረሰበት

[19]ደናግሉ ለሁለተኛ ጊዜ ተሰብስበው ሳለ፣
መርዶክዮስ በንጉሡ በር ተቀምጦ ነበር።
[20]አስቴር ግን ልክ መርዶክዮስ እንደ ነገራት
የማን ወገንና የየት አገር ሰው እንደ ሆነች
ደብቃ ነበር፤ ይህ የሆነበት ምክንያት መር
ዶክዮስ በሚያሳድጋት ጊዜ ታደርግ እንደ
ነበረው ሁሉ፣ አሁንም ምክሩን ትከተል ስለ
ነበር ነው።
[21]መርዶክዮስ በንጉሡ በር ተቀምጦ ሳለ፣
በሩን ከሚጠብቁት ከንጉሡ የጦር አለቆች
ሁለቱ ገበታና ታራ ተቈጡ፤ ንጉሥ አርጤ

2፥8 ነህ1፥1፤ አስ1፥2፤ዳን8፥2
2፥9 ዘፍ37፥3፤ 39፥21፤1ሳሙ9፥22-24፤2ነገ25፥30፤አስ 9፥19፤ሕዝ16፥9-13፤ ዳን1፥5
2፥10 ቍ20
2፥12 ምሳ27፥9፤ መሓ1፥3፤ኢሳ3፥24
2፥14 1ነገ11፥3፤ አስ4፥11፤መሓ6፥8፤ ዳን5፥2
2፥15 ዘፍ18፥3፤ 30፥27፤አስ5፥8፤7፥3፤ 8፥5፤9፥29፤መዝ 45፥14
2፥17 ሕዝ16፥9-13
2፥18 ዘፍ40፥20፤ 1ነገ3፥15፤አስ1፥7
2፥19 አስ4፥2፤5፥13
2፥20 ቍ10
2፥21 ዘፍ40፥2፤ አስ1፥12፤3፥5፤5፥9፤ 7፥7

የመጣ ሲሆን፣ ትርጕሙ "ኮከብ" ማለት ነው፤ አንዳንዶቹ ግን ኢሽታር ከተባለች የባቢሎናውያን ሴት ጣዖት ስም የተገኘ ነው ይላሉ (የኤር 7፥18 ማብ ይመ)።

2፥8 *አስቴርም ... ተወሰዳ*፤ አስቴርም ሆነች መርዶክዮስ በዚህ ጕዳይ ላይ ሌላ አማራጭ አልነበራቸውም (ከ2ሳሙ 11፥4 ጋር ያነጻጽሩ)።

2፥9 *የተለየ ምግብ*፤ ቃል በቃል ሲተረጐም "ድርሻዋን" ማለት ነው። አስቴር፣ እንደ ዳንኤልና ጓደኞቹ ሁለት (ዳን 1፥5-10)፣ ስለ ምግብ የተሰጠውን ሕግ አልተከተለችም፤ ምናልባት ይህን ያደረገችው አይሁዳዊ ዜግነቷ እንዳይታወቅ ብላ ሊሆን ይችላል (ቍ 10፡20)። ይህን ያህል ድርሻ ለእርሷ መሰጠቱ የተለየ ቸርነት እንደ ተደረገላት ያመለክታል (1ሳሙ 9፥22-24፤ 2ነገ 25፥29-30፤ ዳን 1፥1-10፤ በተቃ ራኒው ኤር 13፥25)። ከዮሴፍ ታሪክ ጋር ለማገናዘብ፣ ከዘፍ 43፥34 ጋር ያነጻጽሩ። ድርሻን መስጠት ወይም ግብር ማብላት ፑሪም በተባለው በዓል አከባበር ውስጥ ትልቅ ድርሻ ያለው አሠራር ሆኖአል (9፥19፡22)።

*2፥10፤* አስቴር ማንነቷን ሁለት ጊዜ እንደ ሰወረች በዚህና በቍ 20 ላይ ተጠቅሷል (በመጽሐፈ አስቴር መግቢያ ላይ "ዓላማው፣ *መሪ ሐሳቡና ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ*" የሚለውን *ይመ*)።

2፥14 *ወደ ሌላው የሴቶች መጠበቂያ ቤት*፤ ቁባቶች ወደ ነበሩባቸው ክፍሎች ማለት ነው።

2፥16 *በሰባተኛው ዓመት ... በዐሥረኛው ወር*፤ ታህሣሥ 479 ዓ.ቅ.ክ ወይም ጥር 478 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው (የ1፥3-4፤ 2፥1 ማብ ይመ)። አስቴር በንግሥትነት ማዕረጓ እስከ 473 ዓ.ቅ.ክ ድረስ እንደ ቀጠለች በመጽሐፉ ውስጥ ባሉት ሁነቶች ላይ ይታ ያል (3፥7 እና ማብ ይመ፤ በተጨማሪም 8፥9-13፤ 9፥1 ይመ)። ከዚህ በኋላ ግን በአጭር ጊዜ ውስጥ ምናልባት ሞታለች ወይም ድን ገት ክብሯን አጥታለች (የ1፥11 ማብ ይመ)።

2፥18 *በዓሉም*፤ ይህ ለመግለጽ የገባው የዕብራይስጡ ቃል በዚህ ቍጥር ላይ የተለየ ትርጕም ያለው ሲሆን፣ የቀረጥ መነሣ ትን፣ የባሪያ ነጻነትን፣ የዕዳ መሰረዝን ወይም የውትድርና አገል ግሎት ግዴታ መቅረትን የሚያመለክት ነው።

*2፥19፤* በመጽሐፈ አስቴር መግቢያ ላይ "ዓላማው፣ መሪ ሐሳቡና ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ" የሚለውን ይመ። የቅምጦቹ ቍጥር ያለ ገደብ እየጨመረ የሄደ ይመስላል። ምናልባት የሴቶ ቹን ለሁለተኛ ጊዜ መሰብሰብና ንጉሡን ለመግደል የተደረገ ውን ሤራ የሚያገናኝ አንድ ምክንያት ይኖር ይሆናል (ቍ21-23)። አንዳንድ ሰዎች ከሥልጣን የወረደችውን ንግሥት አስጢ ንን ለመደገፍ፣ ለቤተ መንግሥቱ ቅርብ የሆኑ ሰዎች የፈጠሩት አድማ ሊሆን ይችላል ብለው ያምናሉ። *በንጉሡ በር*፤ የጥንት ከተማ ቅጥር መግቢያ በሮች ዋነኛ የንግድና የሕግ ነክ ጕዳዮች ማዕከል ነበረ። ገበያዎች የሚካሄዱት በከተማ በር ላይ ነበር፣ የችሎት ሥራም የሚከናወነው በከተማው በር ላይ ነበር (ዘዳ 21፥18-20፤ ኢያ20፥4፤ ሩት4፥1-11፤ መዝ69፥12 ይመ)። የንጉሥም ጉባኤ የሚጠራው በከተማው በር ላይ ነበረ (2ሳሙ 19፥8፤ 1ነገ 22፥10 ይመ)። ዳንኤል መላውን ባቢሎን ያስተዳድር የነበረው በንጉሡ በር ላይ ተቀምጦ ነበር (ዳን 2፥48-49)። መር ዶክዮስ በንጉሡ በር ላይ መቀመጡ በንጉሠ ነገሥቱ ግዛት አስተዳደር ውስጥ ትልቅ ሹመት እንደ ነበረው ያረጋግጣል (የቍ5 ማብ ይመ)። በዚህ ሁሉንም ነገር ለማየት በሚያስችለው ቦታ ላይ ሆኖ ንጉ ሡን ለመግደል የተሸረበውን ሤራ ለመስማት ችሎአል።

*2፥21-23፤* ከዮሴፍ ታሪክ ጋር የሚነጻጸርበት ሌላው

ከስስንም ለመግደል ዶለቱ:: 22መርዶክዮስም
አድማውን ስለ ደረሰበት፣ ለንግሥት አስ
ቴር ገለጠላት፤ እርሷም ይህን ከመርዶክዮስ
ማግኘቷን ለንጉሡ ገልጣ ነገረችው:: 23ነገሩ
ሲጣራም እውነት ሆኖ ተገኘ፤ ሁለቱም ሹማ
ምት በስቅላት ሞት ተቀጡ:: ይህ ሁሉ
በንጉሡ ፊት በታሪክ መዝገብ ተጻፈ::

## ሐማ አይሁድን ለማጥፋት የሸረበው ሤራ

3 ከዚህም ነገር በኋላ ንጉሥ አርጤክስስ
የአጋጋዊውን የሐመዳቱን ልጅ ሐማን
ከፍ ከፍ አደረገው፤ ከሌሎቹም መኳንንት
ሁሉ ከፍተኛውን ሥልጣን በመስጠት
አከበረው:: 2ንጉሡ ስለ እርሱ ይህ እንዲደረ
ግለት አዞ ስለ ነበር፣ በንጉሡ በር ያሉት
የመንግሥቱ ሹማምት ሁሉ ለሐማ ተንበ
ርክከው እጅ በመንሣት አክብሮታቸውን
ይገልጡለት ነበር:: መርዶክዮስ ግን ወድቆ
አልሰገደለትም፤ አክብሮትም አላሳየውም::
3ታዲያ በንጉሡ በር ያሉት የንጉሡ
አገልጋዮች መርዶክዮስን፣ "የንጉሡን ትእ
ዛዝ ለምን ትተላለፋለህ?" ሲሉ ጠየቁት::
4ይህንንም በየቀኑ ይነግሩት ነበር፤ እርሱ
ግን አልተቀበላቸውም:: አይሁዳዊ መሆኑን
ነግሮአቸው ስለ ነበር፣ የመርዶክዮስ ባሕ
ርይ እስከ መቼ ሊቀጥል እንደሚችል ለማ
የት ሲሉ ይህንኑ ለሐማ ነገሩት::
5ሐማም መርዶክዮስ ወድቆ እንዳልሰገደ
ለትና እንዳላከበረው ሲያይ እጅግ ተቈጣ::
6ይልቁንም መርዶክዮስ ከእነማን ወገን
መሆኑን በተረዳ ጊዜ፣ መርዶክዮስን ብቻ
መግደል እንደ ኢምንት ቈጠረው፤ ስለዚህ
ሐማ በመላው የአርጤክስስ መንግሥት
ውስጥ የሚገኙትንና የመርዶክዮስ ወገን
የሆኑትን አይሁድ ሁሉ ለማጥፋት ዘዴ
ፈለገ::
7ንጉሥ አርጤክስስ በነገሠ በዐሥራ ሁለ
ተኛው ዓመት ኒሳን በተባለው በመጀመሪ
ያው ወር፣ ቀኑንና ወሩን ለመለየት ፉር
የተባለ ዕጣ ሐማ ባለበት ጣሉ፤ ዕጣውም
አዳር በተባለው በዐሥራ ሁለተኛው ወር
ላይ ወደቀ::
8ከዚያም ሐማ ንጉሥ አርጤክስስን እንዲህ
አለው፤ "በአሕዛብ መካከል በመንግሥትህ
አውራጃዎች ሁሉ ተሠራጭቶና ተበታትኖ
የሚኖር አንድ ሕዝብ አለ፤ ይህም ሕዝብ

2፥23 ዘፍ40፥19፤ ዘዳ21፥22-23፤አስ 6፥1፤10፥2፤6፥2፤ መዝ7፥14-16፤ምሳ 26፥27፤መክ10፥8
3፥1 ዘፀ17፥8-16፤ ዘኍ24፥7፤ዘዳ25፥17-19፤1ሳሙ14፥48
3፥3 አስ5፥9፤ ዳን3፥12
3፥4 ዘፍ39፥10
2፥5 አስ2፥21
3፥6 አስ9፥24፤መዝ 74፥8፤83፥4፤ምሳ 16፥25
3፥7 ቍ13፤ዘሌ 16፥8፤1ሳሙ10፥21፤ አስ9፥24: 26፤9፥19
3፥8 ዕዝ4፥15፤ኤር 29፥7፤ዳን6፥13፤ሐሥ 16፥20-21

ምክንያት ሁለት የንጉሡ አገልጋዮች በትረካው ውስጥ መካተታቸው ነው (ዘፍ 40፥1-3፤ የቍ 3-4 ማብ ይመ)::

2፥23 *በስቅላት፤* በጥንት መካከለኛው ምሥራቅ በተገኙት ሥዕሎችና ሐውልቶች እንዲሁም በግሪካዊው የጥንት ታሪክ ጸሓፊ በሄሮዶቱስ እንደ ተረጋገጠው፣ በፋርስ ሰዎች ዘንድ ወንጀለኛ የሚቀጣው ጭንቅላቱን በሹል ምሰሶ ላይ በመሰካትና በማንጠልጠል ነበር:: እንደ ሄሮዱቱስ አገላለጽ ንጉሥ ዳርዮስ ቀዳማዊ ባቢሎንን በያዘ ጊዜ፣ 3,000 ባቢሎናውያንን በዚሁ መንገድ በሹል ግንድ አናት ላይ በመሰካት ፈጅቶአል፤ ዳርዮስ ራሱ ይህን ድርጊቱን "ቢሒፁን" ከተባለ ቦታ በተገኘው ሰሌዳ ላይ በተቀረጸ ጽሑፉ መዝግቦት ተገኝቶአል:: በእስራኤላውያንና በከነዓናውያን ልማድ ግን ይህ ዘዴ አንድን ወንጀለኛ የመግደያ መንገድ ሳይሆን፣ በሌላ መንገድ የተገደለውን ሰው ሬሳ ወስዶ በማንጠልጠል ለመቀጣጫ እንዲሆን ነው (ዘዳ 21፥22-23፤ ኢያ 8፥29፤ 10፥26፤ 1ሳሙ 31፥8-10፤ 2ሳሙ 4፥12፤ 21፥9-10):: ስለ ዮሴፍ በሚተርከው ክፍል ውስጥ የተገደለው የፈርዖን አሳላፊ የሞተው በዚሁ በሹል እንጨት ላይ በማንጠልጠል ዘዴ ይመስላል (ዘፍ 40፥19):: የሐማ ወንዶች ልጆች የተገደሉት በሰይፍ ተመተው ቢሆንም፣ በድናቸው ለሌላው መቀጣጫ እንዲሆን በሹል ግንድ ላይ ተንጠልጥሎአል (9፥5-14):: *በታሪክ መዝገብ፤* የመጽሐፈ አስቴር ጸሓፊ ለሥነ ጽሑፍ ውበትና ለሚዛናዊ አቀራረብ ያለውን ጥንቃቄ እዚህ ላይ እናያለን፤ የታሪክ መዝገብ የሚለውን አባባል እንኳ ያስገባው በታሪኩ መጀመሪያ ላይ በዚህ ቦታ፣ በመካከል ላይ (6፥1) እንዲሁም በመጨረሻው ላይ (10፥2) ነው:: የገቢታና የታራ የሤራ ታሪክ በትረካው ውስጥ በተገቢው ስፍራ ላይ "መጥጠም" ለመጽሐፉ የትረካ አቀራረብ ውበትን ከጨመሩት ብዙ ሁናቴዎች ውስጥ የጐላ ድርሻ አለው::

3፥1 *ከዚህም ነገር በኋላ፤* አስቴር ንግሥት እንድትሆን ከተመረጠች አራት ዓመታት ዐልፈዋል (ቍ 7፤2፥16-17):: ሐማ በምን ምክንያት እንደ ተሾመ አለመገለጹ፣ መርዶክዮስ ደግ ሠርቶ ሽልማት አለማግኘቱና (2፥21-23፤ 6፥3 ይመ) ሐማ ምንም ሳይሠራ ወሮታ መቀበሉ ምፀት ያለበት ንጽጽር ይመስ ላል:: *የአጋጋዊውን የሐመዳቱን ልጅ፤* የሐማ ዘር አመጣጥ አከራካሪ ጒዳይ ነው:: ሐመዳቱ የሚለው ስም ከፋርስ የመጣ ነው፤ ምናልባትም ቀጥታ አባቱ ሳይሆን የነገድ አባቱ ሊሆን ይችላል:: "አጋጋዊ" የሚለውም መጠሪያ ሌላ የቅርብ የነገድ አባት ሊሆን ይችላል፤ ወይም የአንድ ያልታወቀ ቦታ ስም ሊሆን ይችላል:: ያም ሆነ ይህ፣ ከአማሌቃውያን ንጉሥ ከአጋግ ስም ጋር የተያያዘና እርሱኑ የሚያመለክት ይመስላል (1ሳሙ 15፥20):: የአማሌቅ ሰዎች እስራኤላውያንን ከግብፅ ወጥተው በጒዞ ላይ ሳሉ የመቷቸው ሕዝቦች ናቸው:: (ዘፀ 17፥8-16፤ 1ሳሙ 14፥47-48)፤ በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር "አማሌቃውያንን ከትውልድ እስከ ትውልድ ጠላት ሆኖ ይወጋቸዋል" (ዘፀ 17፥6):: እስራኤልም ይህን አድራጎት አለመርሳት ብቻ ሳይሆን፣ "የአማሌቅን መታሰቢያ ከሰ ማይ በታች ማስወገድ" ይኖርባታል (ዘፀ 25፥17-19):: ሳኦል አማሌቃውያንን ለማጥቃት ባደረገው ውጊያ (1ሳሙ 15)፣ የአማሌቃውያንን ንጉሥ ገድሎአል፤ ከዚህም በተጨማሪ ሁሉንም ባይሆን (1ዜና4፥ 42-43)፣ የኩተማውን ሕዝብ በአብዛኛው ፈጅቶአል:: በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ እንደምናየው፣ ብንያማዊው ሳኦል ጦርነት ካደረገባቸው ከአምስት መቶ ዓመታት በኋላ፣ ብንያማዊው መርዶክዮስ (የ2፥5 ማብ ይመ) ከአማሌቃውያን ጋር ጦርነቱን ይቀጥላል::

*3፥2-6፤* የአይሁድ ሕዝብ ለነገሥታትና (1ሳሙ 24፥8፤ 2ሳሙ 14፥4፤ 1ነገ 1፥16 ይመ) ለሌሎችም ሰዎች (ዘፍ 23፥7፤ 33፥3፤ 44፥14) በግምባራቸው ተደፍተው እጅ ይነሡ ስለ ነበር፣ መርዶክዮስ ለሐማ ወድቆ እጅ ያልነሣው፣ ሁለተኛውን የአሪት ሕግ ትእዛዝ (ዘፀ 20፥4) ለማክበር ብሎ አልነበረም:: መርዶክዮስ እጅ ያልነሣውና ሐማም የአይሁድን ሕግ ከምድር ገጽ ለማጥፋት ቈርጦ የተነሣው (ቍ 5-6) በአይሁድ ሕዝብና በአማሌቃውያን መካከል በነበረው የረጅም ዘመን ጥላቻ መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም:: "በመላው ... መንግሥት ውስጥ የሚገኙትን... አይሁድ" (ቍ6) ለማጥፋት የተደረገው ሙከራ የእግዚአብሔርን የማዳን ዕቅድ ለማጥፋት የተደረገ ሙከራ ነው (በመግቢያው ላይ "ዓላማው፣ መሪ ሐሳቡና ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ" የሚለውን ይመ)::

*3፥4፤* አባባሉን በዮሴፍ ታሪክ ውስጥ ካለው አገላለጽ ጋር ያነጻጽሩ (ዘፍ 39፥10)::

3፥7 *በዐሥራ ሁለተኛው ዓመት ... በመጀመሪያው ወር፤* ሚያዝያ ወይም ግንቦት ወር 474 ዓ.ቅ.ክ ሲሆን፣ የአስቴር ንግሥትነት አምስተኛ ዓመት ነው:: *ዕጣ... ጣሉ፤* ዕጣውን የጣሉት ሰዎች ማንነት አይታወቅም፤ ሆኖም ሐማን የሚረዱ ኮከብ ቈጣሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ (5፥10:14፤ 56፥12-13):: *ፉር፤* 9፥24:26 ይመ:: ይህ ቃል በአካዳውያን ጽሑፍም ውስጥ "ዕጣ" የሚል ትርጒም ይዞ ይገኛል:: ፑሪም የሚባለው ክብረ በዓል የመጣው ከዚሁ ቃል የብዙ ቍጥር ነው (9፥23-32 ይመ):: የአይሁድ ሕዝብ ከግብፅ የወጡበትን የፋሲካ በዓል በሚያከብሩበት ወር ሐማ ከምድር ገጽ ሊያጠፋቸው መወጠኑ፣ ምስጢር አዘል ሁኔታ ይታይበታል (ዘፀ 12፥1-11):: *በዐሥራ ሁለተኛው ወር፤* ዕዋጁ ወጥቶ በተግባር ላይ እስኪውል ድረስ ዐሥራ አንድ ወር ያህል እንደ ወሰደ ይገመታል፤ ምክንያቱም ዕዋጁ ሥራ ላይ የዋለው በአዳር ወር (የካቲት/መጋቢት) ነበር::

*3፥8-9፤* በዚህ ሐሰትና እውነት በተደበላለቀበት አባባል ውስጥ ሐማ ሊያጠፋው የፈለገው ሕዝብ ስም ሆን ተብሎ ተደብቆአል፤ የአይሁድ ሕዝብ በእርግጥ የራሳቸው ባህልና ሕግ ያላቸው ናቸው፤ ዳሩ ግን ለንጉሡ የማይታዘዙ አልነበሩም (ኤር 29፥7)::

3፥8 *ተሠራጭቶና ተበታትኖ፤* 8፥11:17፤ 9፥2:12:16: 19-20:28 ይመ::

ከሌሎች ሕዝቦች ሁሉ የተለየ ልማድ ያለው ና የንጉሡንም ሕግ የማይታዘዝ ነው፤ ታዲያ ይህን ሕዝብ ዝም ማለቱ ለንጉሡ አይበጅም:: 9ነገሩ ንጉሡን ደስ የሚያሰኘው ከሆነ፣ እነርሱን ለማጥፋት ዐዋጅ ይውጣ፤ እኔም ይህን ተግባር ለሚፈጽሙ ሰዎች የሚውል ዐሥር ሺህ መክሊት ብር ወደ መንግሥት ግምጃ ቤት አስገባለሁ::”

10ስለዚህ ንጉሡ የቀለበት ማኅተሙን ከጣቱ አውልቆ የአይሁድ ጠላት ለሆነው ለአጋጋዊው ለሐማዳቱ ልጅ ለሐማ ሰጠው:: 11ንጉሡም ሐማን፣ “ገንዘቡን እዚያው ያዘው፤ ሕዝቡንም እንዳሻህ አድርገው” አለው::

12ከዚያም በመጀመሪያው ወር ዐሥራ ሦስተኛው ቀን የንጉሡ ጸሐፊዎች ተጠሩ:: እነርሱም የሐማን ትእዛዝ በሙሉ በየአውራጃው ፊደልና በየሕዝቡ ቋንቋ፣ ለንጉሡ እንደራሴዎች፣ ለልዩ ልዩ አውራጃ ገዦችና ለልዩ ልዩ ሕዝቦች መኳንንት ጻፉ:: ይህም የተጻፈው በራሱ በንጉሡ አርጤክስስ ስም ሲሆን፣ የታተመውም በራሱ ማኅተም ነበር:: 13አዳር በተባለው በዐሥራ ሁለተኛው ወር፣ በዐሥራ ሦስተኛው ቀን ወጣት፣ ሽማግሌ፣ ሴትና ሕፃን ሳይባል አይሁድ ሁሉ በዚያኑ ዕለት እንዲጠፉ፣ እንዲገደሉና እንዲደመሰሱ፣ ሀብታቸውም እንዲዘረፍ ደብዳቤ ለንጉሡ አውራጃዎች ሁሉ በመልእክተኞች እጅ ተላከ:: 14ለእያንዳንዱም አውራጃ ሕዝብ እንዲታወቅ፣ እነርሱም ለዚያ ቀን ዝግጁ እንዲሆኑ፣ የዋናው ዐዋጅ ቅጅ ሕግ እንዲወጣና ወደ እያንዳንዱም አውራጃ እንዲላክ ተደረገ::

15መልእክተኞቹ በንጉሡ ትእዛዝ ተቻኩለው ወጡ፤ ዐዋጁም በሱሳ ግንብ ተላለፈ:: ንጉሡና ሐማ ለመጠጣት ተቀመጡ፤ የሱሳ ከተማ ግን ግራ ተጋብታ ነበር::

### መርዶክዮስ የአስቴርን ርዳታ ጠየቀ

4 መርዶክዮስ የተደረገውን ሁሉ ባወቀ ጊዜ፣ ልብሱን ቀደደ፤ ከዚያም ማቅለብሶ፣ በራሱ ላይ ዐመድ ነስንሶ ድምፁን ከፍ በማድረግ አምርሮ እየጮኸ ወደ ከተማዪቱ መካከል ወጣ:: 2ማቅ የለበሰ እንዲገባ ስለማይፈቀድለት፣ የሄደው እስከ ንጉሡ በር ድረስ ብቻ ነበር:: 3የንጉሡ ዐዋጅና ትእዛዝ በደረሰበት አውራጃ ሁሉ፣ በአይሁድ መካከል ታላቅ ሐዘን ሆነ፤ ጾሙ፤ አለቀሱ፤ ጮኹም:: ብዙዎቹም ማቅና ዐመድ ላይ ተኙ::

4የአስቴር ደንገጡሮችና ጃንደረቦች መጥተው ስለ መርዶክዮስ በነገሯት ጊዜ፣ እጅግ አዘነች፤ እርሷም በማቁ ፈንታ የሚለብሰውን ልብስ ላከችለት፤ እርሱ ግን አልተቀበላቸውም:: 5ከዚያም አስቴር ከንጉሡ ጃንደረቦች መካከል እርሷን እንዲያገለግል የተመደበውን ሀታክን ጠርታ፣ መርዶክዮስ ምን ችግር እንደ ገጠመውና ስለ ምንስ እንደዚህ እንደ ሆነ እንዲያጣራ ላከችው::

6ስለዚህ ሀታክ በንጉሡ በር ፊት ለፊት ወደሚገኘው ወደ ከተማዪቱ አደባባይ ወደ መርዶክዮስ ወጣ:: 7መርዶክዮስ የደረሰበትን ነገር ሁሉ፣ እንዲሁም ሐማ የአይሁድን ሕዝብ ለማጥፋት ወደ ንጉሡ ግምጃ ቤት ለማግባት ቃል የገባውን የገንዘብ ልክ ጭምር ነገረው:: 8አይሁድን ለማጥፋት በሱሳ የወጣውን የዋናውን ዐዋጅ ቅጅም ለአስቴር እንዲያሳያትና በዝርዝር እንዲያስረዳት ሰጠው፤ ወደ ንጉሡም ዘንድ ገብታ ስለ ሕዝቧ ምሕረት እንድትጠይቅና እንድትማልድ አጥብቆ ይነግራት ዘንድ አሳሰበው::

9ሀታክም ተመልሶ መርዶክዮስ የነገረውን ሁሉ ለአስቴር አስታወቃት:: 10እርሷም ለመርዶክዮስ እንዲህ እንዲለው ነገረችው፤ 11“የንጉሡ ባሮችና በንጉሡ አውራጃዎች የሚገኙ ሰዎች ሁሉ ወንድም ሆነ ሴት፣ ማንም ሰው ሳይጠራ ንጉሡ ወዳለበት ወደ ውስጠኛው አደባባይ የሚገባ፣ ንጉሡ አንድ ሕግ ብቻ እንዳለው ያውቃል፤ ይኸውም እንዲህ ያደረገው ሰው ይገደላል፤

3፥9 አስ7፥4
3፥10 ዘፍ41፥42
3፥12 ዘፍ38፥18፤ ነህ13፥24
3፥13 ቍ7፤1ሳሙ 15፥3፤ዕዝ4፥6፤ አስ8፥11፤9፥10
3፥14 አስ8፥8፤9፥1
3፥15 አስ1፥10፤ 8፥14፡15
4፥1 ዘፀ11፥6፤ ዘኍ14፥6፤2ሳሙ 13፥19፤መዝ30፥11፤ ሕዝ27፥30-31
4፥2 አስ2፥19
4፥7 አስ7፥4
4፥11 አስ2፥14፤ 5፥2፤8፥4፤መዝ125፥3፤ ዳን2፥9

3፥9 *ዐሥር ሺህ መክሊት፣* ታሪክ ጸሓፊው ሄሮዱቱስ የፋርስ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ዓመታዊ ገቢ 15,000 መክሊት እንደ ሆነ ይናገራል:: እንግዲህ እዚህ ላይ የተጠቀሰው አኃዝ ትክክል ከሆነ፣ ሐማ ያቀረበው የዓመቱን ገቢ ሁለት ሦስተኛ መሆኑ ነው፤ ይህ ደግሞ ከፍተኛ ወጪ ነው:: ምናልባት ሐማ ያሰበው የአይሁድን ሕዝብ ሀብት ንብረት በመውረስ ሊሰጠው ይሆናል:: አቀራረቡም የጉቦ መልክ አለው:: በአንድ በኩል አይሁድን በማጥፋት ዘመቻ ላይ የሚሳተፉ ሰዎች እግረ መንገዳቸውን የአይሁድን ሕዝብ እንዲዘርፉ የተፈቀደላቸው ይመስላል (ቍ13)፤ ይህም የገንዘብ ክፍያ በማግኘት ዐዋጁን ተግባር ላይ ለማዋል የሚያበረታታቸው ሊሆን ይችላል፤ አርጤክስስ ሕዝቡንና ገንዘባቸውን አሳልፎ ሰጥቶአል:: በሌላ በኩል ደግሞ 4፥7 እና 7፥4 ላይ እንደሚታየው፣ ንጉሡ ገንዘብ ለመሰብሰብ ያቀደ ይመስላል:: *ይህን ተግባር ለሚፈጽሙ ሰዎች፤* ይህ ሐረግ የሚገልጸው ምናልባት የገቢ ቀረጥ ሰብሳቢዎችን ወይም ዐዋጁን በተግባር የሚፈጽሙትን ሰዎች በአጠቃላይ ይሆናል:: አማሌቃውያን ከዚህ ቀደም ሲል፣ እስራኤላውያንን ምርኮኛ አድርገው በዝብዘዋቸው ነበር (የቍ1 ማብ ይመ):: ሐማ ያቀደው ታሪክ ለመድገም ነበር::

3፥12 *በመጀመሪያው ... በዐሥራ ሦስተኛው ቀን፤* ይኸውም በንጉሥ አርጤክስስ ዐሥራ ሁለተኛ የግዛት ዘመን ማለት ነው (ቍ 7)፤ ይህም ሚያዝያ 474 ዓ.ቅ.ክ ይሆናል::

*3፥13፤* ሐማ በእስራኤል ላይ ያሳወጀው የጥፋት ርምጃ ቀደም ሲል እስራኤላውያን በአማሌቃውያን ላይካወጁት ጥፋት ጋር ተመሳሳይ ነው (1ሳሙ 15፥3):: *በዐሥራ ሁለተኛው ወር በዐሥራ ሦስተኛው ቀን፤* በመጋቢት ወር 473 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው (8፥12 ይመ)::

*3፥15፤* ሐማና ንጉሡ በትረካው ውስጥ የአይሁድን ሕዝብ ዕድል ፈንታ በሚወስን ጉዳይ ላይ እንደ ገና ለማጋር አንድ ላይ ተቀምጠው ከወይኑ ይጠጣሉ (7፥1-2)፤ ነገር ግን ያ ጊዜ የግንኙነታቸው ማከተሚያና ዐዋጁ ተገልብጦ ሁሉም ነገር በተቃራኒው የሚታይበትና ሁኔታዎች የሚለዋወጡበት ጊዜ ሊሆን ነው:: እዚህ ላይ የሚታየውን ፈንጠዝያ የአይሁድ ሕዝብ ከጾሙበትና ከዐዘኑበት ሁኔታ ጋር ሲታይ፣ እጅግ የተራራቀና የተቃረነ ሆኖ እናገኘዋለን (4፥1-3፡15-16)::

4፥2 *ንጉሡ በር፤* የ2፥19 ማብ ይመ::

*4፥3፤* የ3፥15 ማብ ይመ:: በመጽሐፈ አስቴር ውስጥ ጐልተው የሚታዩት ግብዣዎች በቍ 3፡6 ላይ ከተጠቀሱት የጾም ጊዜያት ጋር ሲነጻጸሩ ትኩረት የሚስቡ ናቸው፤ ሁለቱ የጾም ጊዜያት ከሁለቱ የፈንጠዝያ ጊዜያት ጋር የሚገናዘቡ ናቸው (የ9፥31 ማብ ይመ)::

*4፥4-12፤* አስቴርና መርዶክዮስ በሀታክ አማካይነት መነጋገራቸው፣ መርዶክዮስ የሐዘን ልብስ ለብሶ ወደ ቤተ መንግሥቱ ሕንጻ ለመግባት እንደ ተከለከለና (ቍ2)፣ አስቴርም ብትሆን ከሴቶቹ መጠበቂያ ክፍሎች እንዳትርቅ ገደብ የተጣለባት መሆኑን ያመለክታል::

*4፥7፤* የ3፥9 ማብ ይመ:: ሐማ ለንጉሡ እሰጣለሁ ብሎ ቃል የገባውን የገንዘብ መጠን መርዶክዮስ ማወቅ መቻሉ፣ በሱሳ ቤተ መንግሥት ውስጥ ከፍተኛ ስፍራ እንደ ነበረው ያመለክታል (2፥21-23)::

4፥8 *ስለ ሕዝቧ፤* ሀታክ እዚህ ላይ አስቴር አይሁዳዊት መሆኗን ዐውቆአል ማለት ነው::

*4፥11፤* ሄሮዱቱስ የተባለው ታሪክ ጸሓፊ፣ ሳይጠራ ንጉሡ

አንድ ሰው ከእንዲህ ዐይነቱ ሞት የሚተር
ፈው፣ ንጉሡ የወርቅ ዘንጉን ሲዘረጋለት
ብቻ ነው:: እኔ ግን ወደ ንጉሡ ዘንድ
እንድገባ ከተጠራሁ ከሠላሳ ቀን በላይ
ሆነ::"

12የአስቴር ቃል ለመርዶክዮስ በተነገረው
ጊዜ፣ 13ይህን መልስ ላከባት፤ "አንቺ በን
ጉሥ ቤት በመሆንሽ ብቻ ሌላው የአይሁድ
ሕዝብ ሲጠፋ አንቺ የምትተርፊ እንዳይመስ
ልሽ፤ 14በዚህ ጊዜ አንቺ ዝም ብትዪ፣ ለአይ
ሁድ ርዳታና ትድግና ከሌላ ስፍራ ይመጣ
ላቸዋል፤ አንቺና የአባትሽ ቤት ግን ትጠፋ
ላችሁ፤ ደግሞስ አንቺ ንግሥት ለመሆን
የበቃሽው ለዚህ ጊዜ እንደ ሆነ ማን ያው
ቃል?"

15ከዚያም አስቴር ለመርዶክዮስ ይህን
መልስ ላከችበት፤ 16 "ሂድና በሱሳ ያሉትን
አይሁድ ሁሉ በአንድነት ሰብስብ፤ ስለ
እኔም ጹሙልኝ፤ ቀንም ይሁን ሌሊት ለሦ
ስት ቀን አትብሉ፤ አትጠጡም:: እኔና ደን
ገጡሮቼም እናንተ እንደምታደርጉት ሁሉ
እንጾማለን፤ ይህ ከተፈጸመ በኋላ ግን ነገሩ
ምንም እንኳ ከሕግ ውጭ ቢሆንም፣ ወደ
ንጉሡ ዘንድ እሄዳለሁ፤ ከጠፋሁም ልጥፋ::"

17ስለዚህ መርዶክዮስ ሄደ፤ የአስቴርንም
ትእዛዝ ሁሉ ፈጸመ::

### አስቴር ለንጉሡ ያቀረበችው ልመና

5 በሦስተኛው ቀን አስቴር የክብር ልብ
ሷን ለብሳ በንጉሡ አዳራሽ ፊት ለፊት
ባለው በቤተ መንግሥቱ ውስጠኛ አደባባይ
ገብታ ቆመች:: ንጉሡም አዳራሹ ውስጥ
በመግቢያው ትይዩ በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ
ነበር:: 2ንግሥት አስቴር በአደባባዩ ላይ ቆማ
ሲያያት ደስ አለው፤ በእጁ የያዘውን የወ
ርቅ ዘንግ ዘረጋላት፤ አስቴርም ቀረብ ብላ
የዘንጉን ጫፍ ነካች::

3ከዚያም ንጉሡ፣ "ንግሥት አስቴር ሆይ፤
ለምን መጣሽ? ከእኔ የምትፈልጊውስ ምን
ድን ነው? እስከ መንግሥቴ እኩሌታ እንኳ
ቢሆን ይሰጥሻል" አላት::

4አስቴርም መልሳ፣ "ንጉሡን ደስ የሚያ
ሰኘው ቢሆን፣ ባዘጋጀሁለት ግብዣ ላይ
ንጉሡ ዛሬ ከሐማ ጋር ይገኝልኝ" አለች::

5ንጉሡም፣ "አስቴር ያለችውን እንድንፈ
ጽም፣ ሐማን በፍጥነት ጥሩት" አለ:: ስለ
ዚህ ንጉሡና ሐማ አስቴር ወዳዘጋጀችው
ግብዣ ሄዱ:: 6የወይን ጠጅ እየጠጡ ሳለ
ንጉሡ ዳግመኛ አስቴርን፣ "እስቲ የምትፈ
ልጊው ምንድን ነው? ይሰጥሻል፤ ደግሞስ
የምትጠዪቂው ምንድን ነው? እስከ መንግ
ሥቴ እኩሌታ እንኳ ቢሆን ይፈቀድልሻል"
አላት::

7አስቴርም እንዲህ ስትል መለሰች፤
"ልመናዬም፣ ጥያቄዬም ይህ ነው፤ 8በንጉሡ
ዘንድ ሞገስ ካገኘሁና የምፈልገውን ሊሰጠ
ኝና ልመናዬንም ሊፈጽምልኝ ንጉሡን ደስ
ካሰኘው፣ ንጉሡና ሐማ በማዘጋጅላቸው ግብዣ
ላይ ነገ ይገኙልኝ:: ከዚያም እኔ ለንጉሡ
ጥያቄ መልስ እሰጣለሁ::"

### ሐማ በመርዶክዮስ ላይ ያወረደው ቍጣ

9ሐማ በዚያን ቀን ደስ ብሎትና መን
ፈሱ ረክቶ ወጣ፤ ነገር ግን መርዶክዮስን
በንጉሡ በር ላይ ሲያየው ከተቀመጠበት
አለመነሣቱንና በፊቱም አለመንቀጥቀጡን
ሲመለከት፣ ቍጣው በመርዶክዮስ ላይ
ነደደ:: 10ሐማ ግን እንደ ምንም ራሱን
ተቈጣጥሮ ወደ ቤቱ ሄደ::

ወዳጆቹንና ሚስቱን ዞሳራን አስጠርቶ
በአንድነት ከሰበሰባቸው በኋላ፣ 11ሐማ ስለ
ሀብቱ ታላቅነት፣ ስለ ልጆቹ ብዛት እንዲ
ሁም ንጉሡ የቱን ያህል እንዳከበረው፣
ከሌሎቹም መኳንንትና ሹማምት ይበልጥ
እንዴት ከፍ ከፍ እንዳደረገው እያጋነነ ነገ
ራቸው:: 12ሐማም፣ "ምን ይኸ ብቻ" አለ፤
"ንግሥት አስቴር ባዘጋጀችው ግብዣ ላይ
ከንጉሡ ጋር እንድገኝ የጋበዘችው ሰው

4፥14 ዘፍ45፥7፤ 50፥20፤ዘዳ28፥29፤ አስ9፥16:22፤ኢዮ 34፥29፤መዝ28፥1፤35 ፥22፤መክ3፥7፤ኢሳ 42፥14፤57፥11፤62፥1 ፤64፥12፤አሞ5፥13
4፥16 ዘፍ43፥14፤ 2ዜና20፥3፤አስ9፥31
5፥1 ምሳ21፥1፤ሕዝ 16፥13
5፥2 አስ4፥11
5፥3 አስ7፥2፤ ዳን5፥16፤ማር6፥23
5፥6 አስ1፥10፤9፥ 12፤ዳን5፥16፤ማር 6፥23
5፥8 አስ2፥15፤ 1ነገ3፥15
5፥9 አስ2፥21፤3፥3፤ ምሳ14፥17
5፥10 አስ6፥13
5፥11 አስ9፥10:13፤ ምሳ13፥16
5፥12 ኢዮ22፥29፤

ዘንድ ለመቅረብ የሞከረ ማንኛውም ሰው ንጉሡ ወዲያውኑ የተለየ ምሕረት ካላደረገለት በቀር እንደሚገደል ጠቅሶ ጽፎአል::

*4፥12-16፤* የመጽሐፈ አስቴር መሪ ሐሳቦች በዚህ ክፍል ውስጥ በግልጽ ተብራርተዋል:: የአይሁድ ሕዝብ መዳኑ የማይቀር መሆኑን መርዶክዮስ ያመነው፣ እግዚአብሔር ዐላማውን ከግብ ለማድረስም ሆነ የተስፋ ቃሉን ለመጠበቅ ሙሉ ሥልጣን ያለው መሆኑን ከመገንዘቡ የተነሣ ነው:: በአስቴር በኩል እንኳ ባይሳካ፣ የአይሁድ መዳን በሌላ መንገድ መሳካቱ የማይቀር ነው:: ይሁን እንጂ "የሚሆነው ይሆናል፤ የማይሆነው አይሆንም" ከሚል አመለካከት የመጣ አይደለም፤ ምክንያቱም አስቴር ከእርሷ የሚጠበቀውን ካላደረገች እርሷና ቤተ ሰቦቿ ይጠፋሉ:: የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነትና የሰዎችን ተጠያቂነት ከማቴ 26፥24፤ ሐሥ 2፥23 ጋር ያነጻጽሩ::

4፥14 *በዚህ ጊዜ፤* በዘፍ 45፥5-7 ላይ ከሚገኘው ከዮሴፍ ታሪክ ጋር ያነጻጽሩ::

4፥16 *ጹሙልኝ፤* የቍ 3 ማብ ይመ:: ጸሎት ከእንደዚህ ዐይነቱ ጾም ጋር አብሮ ሲሄድ፣ የጾሙ አካል ተደርጎ ይወሰድ ነበር (መሳ 20፥26፤ 1ሳሙ 7፥6፤ 2ሳሙ 12፥16፤ ዕዝ 8፥21-23፤ ነህ 9፥1-3፤ ኢሳ 58፥3፤ ኤር 14፥12፤ ኢል 1፥14፤ 2፥12-17፤ ዮና 3፥6-9 ይመ):: ስለ ጾም እየተናገረ ጸሎትን ወይም የእግዚአብሔርን ስም አያይዞ ያልጠቀሰው ሆን ብሎ ነው፤ ሃይማኖት ነክ የሆኑ ሐሳቦችን ወይም ቃላትን ሳይጨምር፣ ቢታሪኩ ውስጥ እየሠራ ያለው እግዚአብሔር መሆኑን አጕልቶ ማሳየት መቻል ራሱ የተለየ የሥነ ጽሑፍ ዘይቤ ነው (በመግቢያው ላይ "ዐላማው፣ መሪ ሐሳቡና፣ ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ" የሚለውን ይመ)::

*እኔና ደንገጡሮቼም እንጾማለን፤* አስቴርና ደንገጡሮቿ የተለየ ምግብ ለመብላት የታደሉበት ጊዜ ነበር (2፥9)፤ አሁን ደግሞ አብረው ለመጾም ተስማሙ:: *ከጠፋሁም፤* በዮሴፍ ታሪክ ውስጥ ያለውን ተመሳሳይ አቀራረብ ከዚህ ጋር ያነጻጽሩ (ዘፍ 43፥14)::

*5፥2፤* ምሳ 21፥1 ይመ::

*5፥6-7፤* ንጉሡ ሦስት ጊዜ እስኪጠይቃት ድረስ አስቴር መልስ ለመስጠት የዘገየችበትን ምክንያት መገመት እንጂ እርግጠኛ ሆኖ መናገር አይቻልም (ቍ3:6፤7፥2):: ጸሓፊው "የአስቴርን መዘግየት" በመጠቀም ትረካው ልብ እንዳንጠለጠለ ሌላ አዲስ ሐሳብ ያመጣል፤ ያም አዲስ ሐሳብ ሐማ ራሱን ከፍ ከፍ ማድረጉና (ቍ 11-12) መርዶክዮስ ሽልማት ማግኘቱ ናቸው (6፥6-11)::

5፥9፤ *ቍጣው በመርዶክዮስ ላይ ነደደ፤* መርዶክዮስ በግንባሩ ተደፍቶ እጅ ባለመነሣቱ ሐማ እጅግ ተቈጣ፤ ይህም ቀደም ሲል ከተጠቀሰው የመርዶክዮስ እምቢታ ጋር ምፀታዊ ንጽጽር ይታይበታል (3፥2-6)::

5፥11 *ስለ ልጆቹ ብዛት፤* ሐማ ዐሥር ወንዶች ልጆች ነበሩት (9፥7-10):: *ታሪክ ጸሓፊው ሄሮዱቱስ፣* የፋርስ ሰዎች በጦር ሜዳ ጀብዱ ከሠራ ሰው ቀጥሎ ሽልማት የሚሰጡት፣ ብዙ ወንዶች ልጆች ላሉት ሰው እንደ ነበር ጽፎአል፤ የፋርስ ንጉሥ ብዙ ወንዶች ልጆች ላሉት ሰው ሽልማት ይልክ ነበር (ከመዝ 127፥3-5 ጋር ያነጻጽሩ)::

*5፥12-13፤* ምሳ 16፥18፤ 29፥23 ይመ::

አንድ እኔ ብቻ ነኝ፤ ነገም ከንጉሡ ጋር
ጋብዛኛለች:: 13ነገር ግን አይሁዳዊው መር
ዶክዮስ በንጉሡ በር ላይ ተቀምጦ ካየሁት
ይህ ሁሉ እኔን ደስ አያሰኘኝም::"
14ሚስቱ ዞሳራና ወዳጆቹ በሙሉ፣ "ቁመቱ
አምሳ ክንድ^ የሆነ መስቀያ አስተክልና
መርዶክዮስ እንዲሰቀልበት በጠዋት ለንጉሡ
ንገረው፤ ከዚያም ደስ ብሎህ ከንጉሡ ጋር
ወደ ግብዣው ግባ" አሉት:: ይህም ሐሳብ
ሐማን እጅግ ደስ አሰኘው፤ መስቀያውንም
አስተከለ::

## መርዶክዮስ ከፍ ከፍ አለ

6 በዚያች ሌሊት ንጉሡ እንቅልፍ መተ
ኛት አልቻለም:: ስለዚህ በዘመነ መንግ
ሥቱ የተመዘገበው የታሪክ መጽሐፍ ቀርቦ
እንዲነበብለት አዘዘ:: 2በዚያም በሩን ከሚ
ጠብቁት ከንጉሡ የጦር አዛዦች ሁለቱ፣
ገበታና ታራ ንጉሥ አርጤክስስን ለመግ
ደል አሢረው እንደ ነበርና ይህንንም
መርዶ ክዮስ እንደ ተናገረ ተጽፎ ተገኘ::
3ንጉሡም፣ "ታዲያ ይህን በማድረጉ መር
ዶክዮስ ያገኘው ክብርና ማዕረግ ምንድን
ነው?" ሲል ጠየቀ::
የቅርብ አገልጋዮቹም፣ "ምንም አልተደ
ረገለትም" ብለው መለሱ::
4ንጉሡም፣ "በአደባባዩ ማን አለ?" ሲል
ጠየቀ:: በዚህ ጊዜ ሐማ በተከለው ዕንጨት
ላይ መርዶክዮስ ይሰቀል ዘንድ ለንጉሡ
ለመናገር በውጭ በኩል ወደሚገኘው የቤተ
መንግሥቱ አደባባይ ገና መድረሱ ነበር::
5የቅርብ አገልጋዮቹም፣ "እነሆ፤ ሐማ በአ
ደባባዩ ቆሞአል" አሉት::
ንጉሡም፣ "ግባ በሉት" ብሎ አዘዘ::
6ሐማ በገባ ጊዜ ንጉሡ፣ "ንጉሥ ሊያ
ከብረው ለወደደው ሰው ምን ሊደረግለት
ይገባል?" ሲል ጠየቀው::
በዚህ ጊዜ ሐማ፣ "ንጉሡ ከእኔ ይልቅ
የሚያከብረው ማን አለ?" ሲል በልቡ ዐሰበ::

ምሳ16፥18፤29፥23
5፥13 አስ2፥19
5፥14 ዕዝ6፥11፤
አስ7፥9
6፥1 አስ2፥23፤
ዳን2፥1፤6፥18
6፥2 አስ2፥21-23
6፥3 መክ9፥13-16
6፥8 ዘፍ41፥42፤
1ነገ1፥33፤ኢሳ52፥1
6፥9 ዘፍ41፥43
6፥11 ዘፍ41፥42
6፥12 2ሳሙ15፥30፤
አስ7፥8፤ኤር14፥3:4፤
ሚክ3፥7
6፥13 አስ5፥10፤
7፥7፤መዝ57፥6፤ምሳ
26፥27፤28፥18
6፥14 1ነገ3፥15
7፥1 ዘፍ40፥20-22፤

7ስለዚህ ለንጉሡ እንዲህ ሲል መለሰ፤ "ንጉሡ
ሊያከብረው ለወደደው ሰው፣ 8ንጉሡ የሚ
ጐናጸፈው ልብሰ መንግሥት፣ ንጉሡም የሚ
ቀመጥበትና የንጉሡን ዘውድ በራሱ ላይ ያደ
ረገ ፈረስ ይምጣለት:: 9ከዚያም ልብሱና
ፈረሱ እጅግ ከከበሩት ከንጉሡ ልዑላን
መሳፍንት በአንዱ እጅ ይሰጥለት:: ንጉሡ
ሊያከብረው የወደደውን ሰው ያልብሱት፤
በፈረሱም ላይ አስቀመጠውም በከተማዪቱ
ዋና ዋና መንገዶች ላይ እየመሩ፣ 'ንጉሡ
ሊያከብረው ለሚወደው ሰው ይህ ተደርጎለ
ታል'ይበሉ::"
10ንጉሡም ሐማን፣ "በል ፈጥነህ ሂድ፤
ልብሱንና ፈረሱን ውሰድ፤ በንጉሡ በር ላይ
ለሚቀመጠው ለአይሁዳዊው ለመርዶክዮስም
ልክ እንዳልኸው አድርግለት፤ ከተናገርኸውም
አንዳች ነገር እንዳይጐድል" ሲል አዘዘው::
11ስለዚህ ሐማ ልብሱንና ፈረሱን ወስዶ
መርዶክዮስን አለበሰው፤ በዋና ዋና መንገ
ዶች ላይ እየመራም፣ "ንጉሥ ሊያከብረው
ለሚወደው ሰው ይህ ተደርጎለታል" እያለ
በፊቱ ያውጅ ነበር::
12ከዚያም በኋላ መርዶክዮስ ወደ ንጉሡ
በር ተመለሰ፤ ሐማ ግን አዝኖና ራሱን ተከ
ናንቦ በጥድፊያ ወደ ቤቱ ሄደ:: 13የደረሰ
በትንም ሁሉ ለሚስቱ ለዞሳራና ለወዳጆቹ
ሁሉ ነገራቸው::
አማካሪዎቹና ሚስቱ ዞሳራም፣ "በፊቱ
መውደቅ የጀመርህለት መርዶክዮስ ዘሩ ከአ
ይሁድ ወገን ከሆነ፣ ልትቋቋመው አትችልም፤
ያለ ጥርጥር ትጠፋለህ" አሉት:: 14ከእርሱ
ጋር በመነጋገር ላይ ሳሉ፣ የንጉሡ
ጃንደረቦች ደርሰው ሐማን አስቴር ወዳዘጋጀ
ችው ግብዣ አጣደፉት::

## ሐማ ተሰቀለ

7 ስለዚህ ንጉሡና ሐማ ከንግሥት አስቴር
ጋር ለመጋበዝ ሄዱ፤ 2በሁለተኛውም

^14 23 ሜትር ያህል ነው::

5፥14 *አምሳ ክንድ፤* የግንዶቹ ርዝማኔ በግነት መልክ የተ ነገረ ይመስላል:: አንዳንድ ሰዎች ይህን ያህል ርዝመት ያለው ግንድ ከምድር ከፍ አድርጎ ለመስቀል፣ ግንዱ ሕንጻ ላይ (ለምሳሌ በከተማው ቅጥር ላይ) ተተክሎ ይሆናል ይላሉ (1ሳሙ 31፥10 ይመ):: *እንዲሰቀልበት፤* የ2፥23 ማብ ይመ::

*6፥1፤* ይህ ቍጥር በትረካው ውስጥ ቍልፍ ስፍራ አለው:: ሁኔታዎች የከፉ ባይመስሉም፣ ከቁብ የማይቈጠሩ አጋጣሚዎች ታሪኩን ከዳር ለማደርስ ወሳኝ ነጥቦች ናቸው:: የንጉሡ እንቅልፍ ማጣት፣ የታሪክ መዝገቡ እንዲነበብ መጠየቁ፣ መርዶክዮስ በፊት የሠራው በጎ ሥራ የተጻፈበት መዝገብ መታየቱ፣ ሐማ በጠዋት ተነሥቶ ግንዱን በጥድፊያ ማዘጋጀቱ (5፥14)፣ ዘሎ ቤተ መንግሥቱ አደባባይ ውስጥ መግባቱና ንጉሡ ከፍ ከፍ ሊያደርገው የፈለገው እኔን መሆን አለበት ብሎ ማሰቡ፣ በዚህ ታሪክ ውስጥ የተፈጸሙ ክሥተቶችን ሁሉ የሚመራውና የሚቈጣጠረው ልዑል እግዚአብሔር መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው:: ቀደም ሲል ከቁብ ያልተቈጠሩ አጋጣሚዎች ሁሉ እዚህ ላይ ወሳኝ ሚና ያላቸው ሆነው ቀርበዋል:: በዮሴፍ ታሪክ ውስጥ እንደ ታየው (ዘፍ 41፥1-45)፣ የትረካው ዋኛ ገጸ ባሕርይ ዕድል ፈንታ በንጉሡ እንቅልፍ ማጣት ሳቢያ ተቀይሮ ይገኛል (ከዳን 2፥1፤6፥18 ጋር ያነጻጽሩ)::

*6፥2፤* ጸሐፊው በዚያን ጊዜ ያነብ የነበረው ከአምስት ዓመት በፊት ስለ ተፈጸሙ ድርጊቶች ነበር (3፥7 እና 2፥16 ያነጻጽሩ)::

*6፥4-6፤* እዚህም ላይ ምፀታዊ አባባል እንዳለ ግልጽ ነው፤ ሐማ "አንድ ሕዝብ" በማለት የሕዝቡን ማንነት እንደ ሰወረ ሁሉ (3፥8)፣ ንጉሡም እዚህ ላይ ሳያስበው፣ "ንጉሥ ሊያከብረው ለወደደው ሰው" (ቍ6) በማለት ሊከበር የተዘጋጀውን ሰው ማንነት ከሐማ ይሰውራል::

6፥8 *ንጉሡ የሚጐናጸፈው ልብሰ መንግሥት፤* 8፥15 ይመ:: በዘፍ 41፥41-43 ካለው ከዮሴፍ ታሪክ ጋር ያነጻጽሩ:: በጥንት ዘመን የንጉሥ ልብስ ትልቅ ስፍራ ይሰጠው ነበር፤ ልብሱን የለበሰ ሰው የተለየ ክብርና ሞገስ ያገኘ ያህል ይቈጠር ነበር (1ሳሙ 18፥4):: የሌላውን ሰው መጐናጸፊያ መልበስ የዚያን ሰው ኀይል፣ ሥልጣን፣ ክብር ወይም ቅድስና የመካፈል ምልክት ነበር (2ነገ 2፥13-14፤ ኢሳ 61፥3:10፤ ዘካ3፤ ማር 5፥27):: ሐማ ያቀረበው ሐሳብ ያንን ክብር ለሚቀበለው ሰው ትልቅ ልዕልና ከመሆኑም በላይ፣ ንጉሡንም በከፍተኛ ደረጃ የማሞካሸት ሁኔታ ይታይበታል:: ከሀብቱ ይልቅ የንጉሡን ልብስ መልበስ ይመረጥ እንደ ነበረ ያሳያል::

*6፥13፤* በመጽሐፉ ውስጥ የእግዚአብሔር ስም አንድም ቦታ ላይ ባይጠቀስም፣ በሕዝቡ ታሪክ ውስጥ የሚሆነውን ነገር ሁሉ የሚመራው እግዚአብሔር እንደ ሆነ በግልጽ ያሳያል:: የታሪኩ ጸሐፊ የአይሁድን አምላክ ማንም ሊቋቋመው እንደማይችል ተገንዝቦአል::

*6፥14፤* ተጋባዥ እንግዳ ወደ አንድ ድግስ ሲመጣ ማጀብ የተለመደ ነበር (የዮሴፍን ታሪክ በዘፍ43፥15-26 ይመ፤ ከማቴ 22፥1-14 ጋር ያነጻጽሩ)::

ቀን የወይን ጠጅ እየጠጡ ሳለ፣ ንጉሡ
እንደ ገና፣ “ንግሥት አስቴር ሆይ፤ የምት
ለምኚው ምንድን ነው? ይሰጥሻል፤ የም
ትጠይቂውስ ምንድን ነው? እስከ መንግ
ሥቴ እኩሌታ እንኳ ቢሆን ይደረግልሻል”
አላት::
3ከዚያም ንግሥት አስቴር እንዲህ ስትል
መለሰች፤ “ንጉሥ ሆይ፤ በፊትህ ሞገስ አግ
ኝቼና ግርማዊነትህን ደስ የሚያሰኝ ከሆነ፣ ሕይ
ወቴን ታደጋት፤ ልመናዬ ይህ ነው፤ ሕዝ
ቤን አትርፍ፤ ጥያቄዬም ይኸው ነው::
4እኔና ሕዝቤ ለጥፋት፣ ለዕርድና ለመደም
ሰስ ተሸጠናልና:: ወንዶችና ሴቶች ባሮች
ለመሆን የተሸጥን ቢሆን ኖሮ፣ ዝም ባልሁ
ነበር፤ ምክንያቱም እንዲህ ያለው ጭንቀት
ንጉሡን ለማስቸገር የሚበቃ አይደለም[ሐ]::”
5ንጉሥ አርጤክስስም ንግሥት አስቴ
ርን፣ “ለመሆኑ እርሱ ማን ነው? እንዲህ
ያለውን ነገር ለማድረግ እስከዚህ የደፈረ
ውስ ሰው የታለ?” ሲል ጠየቀ::
6አስቴርም፣ “ያ ባላጋራና ጠላት ይህ
ክፉው ሐማ ነው” አለች::
ከዚያም ሐማ በንጉሡና በንግሥቲቱ
ፊት እጅግ ደነገጠ:: 7ንጉሡ ከተቀመጠበት
በቍጣ ተነሣ፤ የወይን ጠጁንም ትቶ ወደ
ቤተ መንግሥቱ የአትክልት ቦታ ሄደ:: ሐማ
ግን ንጉሡ ሊያጠፋው ቈርጦ መነሣቱን
ስላወቀ፣ ንግሥት አስቴር ሕይወቱን እንድ
ታተርፍለት ለመማጠን በዚያው ቀረ::
8ንጉሡ ከቤተ መንግሥቱ የአትክልት
ቦታ ወደ ግብዣው አዳራሽ ሲመለስ አስ
ቴር ደገፍ ባለችበት ድንክ ዐልጋ ላይ ሐማ
ተደፍቶ ነበር::
ንጉሡም፣ “ይባስ ብሎ አብራኝ ያለች
ውን ንግሥት በገዛ ቤቴ ሊደፍራት ያስባ
ልን?” ሲል ተናገረ::
ይህ ቃል ከንጉሡ አፍ ገና እንደ ወጣ፣
የሐማን ፊት ሸፈኑት:: 9ከዚያም ንጉሡን
በቅርብ ከሚያገለግሉት ጃንደረቦች አንዱ
የሆነው ሐርቦና፣ “እነሆ ቁመቱ አምሳ
ክንድ[መ] የሆነ ግንድ በሐማ ቤት አጠገብ
ተተክሎአል፤ ይህን ያዘጋጀው ንጉሡን ለማ
ዳን በጎ ነገር ለተናገረው ለመርዶክዮስ
ነው” አለ::
ንጉሡም፣ “በዚሁ ላይ ስቀሉት” አለ::
10ስለዚህ ለመርዶክዮስ ባዘጋጀው ግንድ
ላይ ሐማን ሰቀሉት፤ ከዚያም የንጉሡ
ቍጣ በረደ::

**ንጉሡ በአይሁድ ስም የተናገረው ዐዋጅ**

8 በዚያኑ ዕለት ንጉሥ አርጤክስስ የአይ
ሁድን ጠላት የሐማን ቤት ንብረት
ለንግሥት አስቴር ሰጣት፤ አስቴርም
መርዶክዮስ እንዴት እንደሚዛመዳት ለንጉሡ
ነግራው ስለ ነበር፣ መርዶክዮስ ወደ ንጉሡ
ዘንድ ቀረበ:: 2ንጉሡ ከሐማ መልሶ የወሰ
ደውን ባለ ማኅተም ቀለበት አውልቆ
ለመርዶክዮስ ሰጠው፤ አስቴርም መርዶክ
ዮስን በሐማ ቤት ንብረት ላይ ሾመ
ችው::
3አስቴር በንጉሡ እግር ላይ ወድቃ በማ
ልቀስ ልመናዋን እንደ ገና አቀረበች::
አጋጋዊው ሐማ በአይሁድ ላይ የሸረበው
ክፉ ሤራ እንዲሽር ለመነችው:: 4ከዚያም
ንጉሡ የወርቅ ዘንጉን ለአስቴር ዘረጋላት፤
እርሷም ተነሥታ በፊቱ ቆመች::
5እንዲህም አለች፤ “ንጉሡን ደስ የሚያሰ
ኘውና እኔም በፊቱ ሞገስ አግኝቼ ከሆነ፣
ጉዳዩም በንጉሡ ዘንድ ተገቢ ሆኖ ከተገኘና
በእኔም ደስ ከተሰኘ፣ የአጋጋዊው የሐመዳቱ

*ሐ4 ወይም፣ ዝም ባልሁም ነበር፤ ነገር ግን ባላጋራችን የሚሰጠው ካሣ ንጉሡ ከሚያጣው ነገር ጋር ከቶ አይነጻጸርም*
መ9 23 ሜትር ያህል ነው::

ማቴ22፥1-14
7፥2 አስ፥10፤5፥3፤9፥12
7፥3 አስ2፥15
7፥4 አስ3፥9፤4፥7
7፥7 ዘፍ34፥7፤ 2ነገ21፥18፤አስ1፥12፤6፥13፤ምሳ19፥12፤20፥1-2
7፥8 ዘፍ34፥7፤39፥14፤አስ1፥6፤6፥12፤ዮሐ13፥23
7፥9 ዘዳ21፥22-23፤አስ1፥10፤5፥14፤መዝ7፥14፡16፤9፥16፤ምሳ11፥5-6፤ማቴ7፥2
7፥10 ዘፍ40፥22፤አስ2፥1፤9፥25፤ምሳ10፥28፤ዳን6፥24
8፥1 ምሳ22፥22-23
8፥2 ዘፍ24፥22፤41፥41፡42፤ምሳ13፥22፤14፥35፤ዳን2፥48
8፥3 ዘፀ17፥8-16
8፥4 አስ4፥11
8፥5 አስ2፥15

*7፥2፤* 5፥3፡6 ይመ::
*7፥3፤* 2፥15፡17 ይመ::
7፥4 *ተሸጠናልና፤* አስቴር እዚህ ላይ የምታወሳው ሐማ
ለንጉሡ ለመስጠት ቃል የገባውን (ጕቦ) ገንዘብ ይመስላል
(3፥9፤ 4፥7)፤ ሐማ ያወጣውንም ዐዋጅ በራሷ አባባል በአጭሩ
ትገልጠዋለች (3፥13):: *እንዲህ ያለው ጭንቀት ንጉሡን...፤* አባ
ባሉ ምናልባት (1) በአይሁድ ሕዝብ ላይ የታቀደው ባርነት ብቻ
ቢሆን ኖሮ፣ በንጉሡ ላይ የሚደርሰው ጉዳት አነስተኛ በሆነ
ነበር፤ ወይም (2) የታሰበው ነገር አይሁድን ባሪያ ለማድረግ ብቻ
ቢሆን ኖሮ፣ አስቴር ንጉሡን ለዚህ ቀላል ነገር ባልጨቀጨቀች
ውም ነበር ለማለት ነው::
7፥8 *አስቴር ደገፍ ባለችበት ድንክ ዐልጋ ላይ ... ተደፍቶ፤*
ምግብ ይበላ የነበረው አነስተኛ መደብ ወይም መለስተኛ ዐልጋ
ላይ ደገፍ በማለት ነበር (አሞ 6፥4-7፤ ዮሐ 13፥23):: አይሁዳ
ዊው መርዶክዮስ በፊቴ ተደፍቶ ለምን እጅ አልነሣኝም በማለት
ድብን ብሎ የነበረው ሐማ፣ እዚህ ላይ በአይሁዳዊቷ በአስቴር
ፊት (6፥13 ይመ) ተደፍቶ መስገዱ ምፀታዊ ትርጕም አለው::
ንጉሡ የነበረበትን አዳራሽ ለቆ መውጣቱ ለሐማ የመጨረሻ ዕጣ
ፈንታ ወሳኝ ሁኔታ ነበር:: *የሐማን ፊት ሸፈኑት፤* 6፥12 ይመ፤
የሐማ ፊት የተሸፈነው ሁለት ጊዜ መሆኑ ነው::
*7፥9፤* አስቴር ከዚህ ቀደም ሲል በዚያኑ ዕለት መርዶክዮስ
ድል እንደ ተቀዳጀ (ም6) የምታውቅ ስለ መሆኗ ፍንጭ የለም፤
ስለ ወገኖቿ በሕይወት መኖር ደጅ ስትጠና ነበር:: ሐርቦና ስለ
መስቀያ ግንዶቹ ማንሣቱ፣ ሐማ ለንጉሡ ባለ ውለታ የነበረውን
መርዶክዮስን ለመግደል መነሣቱን ስለሚጠቍም፣ ተጨማሪ
ወንጀል ሆኖበታል:: *ሐርቦና፤* ስሙ በመጽሐፉ ውስጥ ሁለት ጊዜ
ተጠቅሶአል (1፥10፤ 7፥9)፤ ይህም ከመጽሐፉ ብዙ ሰዎችንና
ሁኔታዎችን ጥንድ አድርጎ ከማቅረብ ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያት
መካከል አንዱ ነው:: ከዚህ ቀደም ሲል ንግሥት አስጢንን እን
ዲያመጣትና የእርሷን ውድቀት፣ ቀጥሎም አስቴር እንድትመ
ረጥ ሁኔታዎችን (1፥10) ያመቻች ነበር፤ አሁን ደግሞ በሐማ
የውድቀትና በመርዶክዮስ የትንሣኤ ታሪክ ውስጥ ዐይነተኛ
ሚና በመጫወት ላይ ነው::
7፥10 *በረደ፤* 2፥1 ይመ:: ሁኔታዎችን በጥንድ መግለጥ
የመጽሐፉ አስቴር ጸሓፊ ዐይነተኛ አቀራረብ እንደ መሆኑ፣
የንጉሡ ቍጣ መብረድ ከዚህ በፊትም በ2፥1 ላይ ተጠቅሶአል::
*8፥1-17፤* የመጽሐፉ አስቴር ጸሓፊ በ3፥1-4፥3 የተጠቀሰ
ውን አባባል ከሞላ ጐደል በተመሳሳይ ቃላት በመድገም የሥነ
ጽሑፉን ይዘት በሚያስደንቅ መልክ ሚዛን እንዲጠብቅ
ያደርጋል::
8፥1 *የሐማን ቤት ንብረት ለንግሥት አስቴር ሰጣት፤*
የግሪኩ ታሪክ ጸሓፊ ሄሮዶቱስና አይሁዳዊው ታሪክ ጸሓፊ
ዮሴፈስ የአንድ ከሓዲ ንብረት ለቤተ መንግሥት ዝ.ንደሚሆን
ጽፈዋል፤ አርጤክስስም የሐማን ንብረት (5፥11) ለአስቴር ሰጠ::
*8፥2፤* ከ3፥10 ጋር ያነጻጽሩ፤ ከንጉሡ እጅ ቀለበቱን
መቀበል ማለት የንጉሡንም ገንዘብ የመጠበቅ ኀላፊነት መቀበል ማለት
ነው፤ እዚህ ላይ መርዶክዮስ የሐማን ሹመትና ሥልጣን ተረክቦአል::
*8፥3-6፤* አስቴርና መርዶክዮስ ደኅንነታቸው ተረጋግጦ
አል፤ ዳሩ ግን የማይሻረው ዐዋጅ አሁንም በተቀረው የአይ
ሁድ ሕዝብ ላይ ሞትን ይዞ እንዳንዣበበ ነው::
8፥3 *አጋጋዊው፤* የ3፥1 ማብ ይመ::
8፥5 *ሞገስ፤* 4፥11፤5፥2 ይመ::

ልጅ ሐማ በንጉሡ አውራጃዎች ሁሉ
የሚገኙትን አይሁድ ለማጥፋት የሸረበውን
ሤራና የጻፈውን ደብዳቤ የሚሽር ትእዛዝ
ይጻፍ:: 6በሕዝቤ ላይ መዐት ሲወርድ እያ
የሁ እንዴት ልታገሥ እችላለሁ? የቤተ
ሰቤንስ መጥፋት እያየሁ እንዴት መቋቋም
እችላለሁ?”

7ንጉሥ አርጤክስስም ለንግሥት አስቴ
ርና ለአይሁዳዊው ለመርዶክዮስ እንዲህ ሲል
መለሰላቸው፤ “እነሆ ሐማ አይሁድን ለማ
ጥፋት ስላቀደ፣ ቤት ንብረቱን ለአስቴር
ሰጥቻለሁ፤ እርሱንም በዕንጨት ላይ ሰቅለ
ውታል:: 8በንጉሥ ስም የተጻፈና በቀለበቱ
የታተመ ደብዳቤ ሊሻር ስለማይችል፣ እና
ንተ ደግሞ አይሁድን በተመለከተ መልካም
መስሎ የታያችሁን ሌላ ዐዋጅ በንጉሡ ስም
ጽፋችሁ በንጉሡ የቀለበት ማኅተም አት
ሙት::”

9ኒሳን በተባለው በሦስተኛው ወር ሃያ
ሦስተኛ ቀን የቤተ መንግሥቱ ጸሓፊዎች
በአስቸኳይ ተጠርተው ነበር፤ እነርሱም
የመርዶክዮስን ትእዛዝ ሁሉ ለአይሁድ፣
እንዲሁም ከህንድ ጀምሮ እስከ ኢትዮ ጵያ
ድረስ፣ በአንድ መቶ ሃያ ሰባት አውራ
ጃዎች ለሚገኙ እንደራሴዎች፣ የአውራጃ
ገዦችና መኳንንት ሁሉ ጻፉ:: እነዚህም
ትእዛዞች የተጻፉት በእያንዳንዱ አውራጃ
ፊደልና በእያንዳንዱ ሕዝብ ቋንቋ፣ እንደ
ዚሁም ለአይሁድ በገዛ ፊደላቸውና በገዛ
ቋንቋቸው ነበር:: 10መርዶክዮስ ትእዛዙን
በንጉሥ አርጤክስስ ስም ጽፎ በንጉሡ የቀ
ለበት ማኅተም አተመው፤ ከዚያም በተለይ
ለንጉሡ በተገሩ ፈጣን ፈረሶች በሚጋልቡ
መልእክተኞች እጅ ላከው::

11የንጉሡም ዐዋጅ በየከተማው የሚኖሩ
አይሁድ ሁሉ እንዲሰበሰቡና ራሳቸውን ከጥ
ቃት እንዲከላከሉ እንዲሁም በራሳቸው፣
በሚስቶቻቸውና በልጆቻቸው ላይ አደጋ የሚ
ያደርስባቸውን የየትኛውንም ዜጋ ወይም
አውራጃ የታጠቀ ኀይል እንዲያጠፉ፣ እን
ዲገድሉ፣ እንዲደመስሱና የጠላቶቻቸውን
ሀብት እንዲዘርፉ ፈቀደላቸው:: 12አይሁድ

8፥6 ዘፍ44፥34
8፥7 ዘዳ21፥22-23
8፥8 ዘፍ38፥18፤ 41፥42፤አስ1፥19፤3፥12-14፤ዳን6፥15
8፥9 ነህ13፥24፤ አስ1፥1
8፥11 ዘፍ14፥23፤ አስ3፥13፤9፥15፡16
8፥12 አስ3፥13፤9፥1
8፥13 አስ3፥14
8፥14 አስ3፥15
8፥15 ዘፍ41፥42፤ አስ3፥15፤9፥4፤10፥2፤2ሳሙ12፥30
8፥16 አስ4፥1-3፤ መዝ97፥10-12፤ 112፥4፤ኢር29፥4-7
8፥17 ዘፀ15፥14፡16፤ዘዳ11፥15፤አስ9፥3፤መዝ35፥27፤45፥15፤51፥8፤ምሳ11፥10፤ዳን6፥26
9፥1 አስ3፥12-14፤8፥12፤ምሳ22፥22-23፤ኢር29፥4-7
9፥2 ዘፍ22፥17፤ መዝ35፥26፤40፥14፤70፥2፤71፥13፡24
9፥3 ዕዝ8፥36፤አስ8፥17

በመላው የንጉሥ አርጤክስስ አውራጃ ሁሉ
ይህን እንዲፈጽሙ የተወሰነው አዳር በተባ
ለው በዐሥራ ሁለተኛው ወር ዐሥራ ሦስ
ተኛ ቀን ነበር:: 13አይሁድ በዚያን ቀን ጠላ
ቶቻቸውን ለመበቀል ዝግጁ እንዲሆኑ፣
የዋናው ዐዋጅ ቅጅ ሕግ ወደየአውራጃው
እንዲላክና የየአገሩም ሕዝብ እንዲያውቀው
ተደረገ::

14በቤተ መንግሥቱ ፈረሶች የተቀመጡ
መልእክተኞችም፣ በንጉሡ አስቸኳይ ትእ
ዛዝ ጋልበው ወጡ፤ ዐዋጁም በሱሳ ግንብ
ተነገረ::

15መርዶክዮስ ሰማያዊና ነጭ የቤተ
መንግሥት ልብስ ለብሶ፣ ትልቅ የወርቅ
አክሊል ደፍቶ፣ ከቀጭን በፍታና ከሐምራዊ
ግምጃ የተሠራ መጐናጸፊያ ተጐናጽፎ
ከንጉሡ ፊት ወጣ፤ የሱሳ ከተማም ደስታ
የተሞላበት በዓል አከበረች:: 16ጊዜውም
ለአይሁድ የደስታና የፈንጠዝያ፣ የተድላና
የክብር ወቅት ሆነላቸው:: 17የንጉሡ ዐዋጅ
በደረሰበት በእያንዳንዱ አውራጃና በእያን
ዳንዱ ከተማ አይሁድ ደስ አላቸው፤ ሐሤት
አደረጉ፤ የፈንጠዝያና የደስታም ቀን ሆነላ
ቸው:: አይሁድን ከመፍራታቸው የተነሣ፣
ከሌሎች አገር ዜጎች ብዙ ሕዝብ አይሁድ
ሆኑ::

### የአይሁድ ድል ማድረግ

9 አዳር በተባለው በዐሥራ ሁለተኛው
ወር ዐሥራ ሦስተኛ ቀን፣ በንጉሡ ትእ
ዛዝ የወጣው ዐዋጅ የሚፈጸምበት ዕለት
ነበር:: በዚህም ዕለት የአይሁድ ጠላቶች
የበላይነቱን እንደሚያገኙ ተማምነው ነበር፤
ሁኔታው ግን ተለወጠና አይሁድ በሚጠሏ
ቸው ላይ የበላይነትን አገኙ:: 2የእነርሱን
መጥፋት በሚፈልጉ ወገኖች ላይ አደጋ
ለመጣል አይሁድ በንጉሥ አርጤክስስ አው
ራጃዎች ሁሉ ባሉት ከተሞቻቸው ተሰበሰቡ::
የሌሎቹ አገር ዜጎች ሕዝብ ሁሉ ፈርተዋቸው
ስለ ነበር፣ ማንም ሊደፍራቸው አልቻለም::
3የየአውራጃው መኳንንት ሁሉ፣ እንደራሴ
ዎች፣ የአውራጃ ገዦች እንዲሁም የንጉሡ
አስተዳዳሪዎች አይሁድን ረዷቸው፤ ይህን

*8፥6፤* ከዮሴፍ ታሪክ ጋር ያነጻጽሩ (ዘፍ 44፥34)::

*8፥8፤* 1፥19 ይመ:: በመግቢያው ላይ “ዓላማው፣ መሪ ሐሳቡና ሥነ ጽሑፋዊ ባሕርያቱ” የሚለውን ይመ:: በትንቢተ ዳንኤል ውስጥ ሜዶናዊውን ዳርዮስን የገጠመው ዐይነት ችግር (ዳን 6፥8፡12፡15) እዚህም ላይ ተከሥቶ እናገኛለን:: መፍትሔውም የመጀመሪያው ሳይሻር፣ ሌላ ተመጣጣኝ ዐዋጅ በማውጣት የቀድሞው እንዳይሠራ ማድረግ ነበር (የ9፥2-3 ማብ ይመ)::

*8፥9-13፤* አባባሉ የተወሰደው በ3፥12-14 ላይ ከሚገኘው ተጓዳኝ ሐሳብ ነው:: የጥፋቱ ስፋትና ክብደት ቀድሞ በአማሌቃውያን ላይ ከታወጀው ጋር ተመሳሳይ ነው (የ3፥13 ማብ ይመ)::

8፥9 *በሦስተኛው ወር ሃያ ሦስተኛ ቀን፤* በአርጤክ ስስ ዐሥራ ሁለተኛ ዓመት የሐማ ዐዋጅ ከወጣ ሁለት ወር ከዐሥር ቀን በኋላ ነበር (የ3፥13 ማብ ይመ)::

8፥12 *በዐሥራ ሁለተኛው ወር ዐሥራ ሦስተኛ ቀን፤* መጋቢት 7 ቀን 473 ዓ.ቅ.ክ ማለት ነው (3፥13 ይመ):: ከመጀመሪያው የፋሪም በዓል በኋላ ዐሥራ አምስት ዓመት ቈይቶ፣ ዕዝራ ወገኖቹን (እስራኤላውያንን) ወደ ኢየሩሳሌም እየመራ ሄዶአል (ዕዝ 7፥9)::

*8፥14-17፤* የክፍሉ ሐሳብ የተወሰደው ከ3፥15-4፥3 ነው::

8፥15 *የቤተ መንግሥት ልብስ፤* መርዶክዮስ በማዕረግ ልብስ ተሸልሞ ሲወጣ ሁለተኛ ጊዜው ነው (6፥10 ይመ)::

*9፥1፤* የ8፥9-13 ማብ ይመ:: የአይሁድ ሕዝብ የመርዶክዮስን ዐዋጅ ከስምንት ወር ከሃያ ቀን በኋላ በተግባር ላይ አዋሉት:: *ሁኔታው ግን ተለወጠና፤* ሁኔታዎች በተቃራኒ መፈጸማቸው፣ የመጽሐፉ ጸሓፊ ለሥነ ጽሑፉ ውበት ምን ያህል እንደሚጠነቀቅ ያመለክ ታል፤ ከትረካው አጋማሽ በፊት የተጠቀሱትን ድርጊቶችና ሁኔታዎች ተቃራኒ በሁለተኛው አጋማሽ ውስጥ በማካተት ለመጽሐፉ ሚዛኑን የጠበቀ ሥነ ጽሑፋዊ ይዘት ይሰጠዋል::

*9፥2-3፤* ይህ የዘፍ 12፥3 ምሳሌ ነው:: የየክፍላተ አገሩ አስተዳዳሪዎች ሁለት የሚቃረኑ ዐዋጆች ሥራ ላይ እንዲውሉ ትእዛዝ ደርሶአቸዋል፤ እነዚህ ሁለት የሚቃረኑ ትእዛዞች ከሐማና ከመርዶክዮስ በንጉሡ ስም የታወጁ ነበሩ፤ አስተዳዳሪዎቹም በወቅቱ በሥልጣን ላይ የነበረውን የመርዶክዮስን ትእዛዝ ተከትለው ሲፈጽሙት ይታያሉ::

ያደረጉትም መርዶክዮስን ስለ ፈሩ ነበር።
4መርዶክዮስ በቤተ መንግሥቱ ታዋቂ ሆነ፤
ዝናው በየአውራጃው ሁሉ ተሰማ፤ ኀይሉም
እየበረታ ሄደ።
5ስለዚህ አይሁድ ጠላቶቻቸውን ሁሉ
በሰይፍ እየመቱ ገደሏቸው፤ አጠፏቸውም፤
በሚጠሏቸውም ላይ ደስ ያላቸውን አደ
ረጉ። 6አይሁድ በሱሳ ግንብ አምስት መቶ
ሰው ገደሉ፤ አጠፉም። 7ፓርሻንዳታን፣ ደል
ፎንን፣ አስፓታን፣ 8ፖራታን፣ አዳልያን፣
አሪዳታን፣ 9ፓርማሽታን፣ አሪሳይን፣ አሪዳ
ይንና ዋይዛታንም ገደሉ፤ 10እነዚህም የአይ
ሁድ ጠላት የሆነው የሐመዳቱ ልጅ የሐማ
ዐሥር ወንዶች ልጆች ነበሩ። በምርኮው
ላይ ግን እጃቸውን አልዘረጉም።
11በሱሳ ግንብ የተገደሉት ሰዎች ብዛት
በዚያኑ ዕለት ለንጉሡ ተነገረው። 12ንጉ
ሡም ንግሥት አስቴርን፣ "አይሁድ በሱሳ
ግንብ አምስት መቶ ሰውና ዐሥሩን የሐማ
ልጆች ገድለዋል፤ አጥፍተዋልም። በተቀሩት
በንጉሡ አውራጃዎችስ ምን አድርገው ይሆን?
አሁንስ የምትለምኚው ምንድን ነው? ይሰ
ጥሻል፤ የምትጠይቂውስ ምንድን ነው?
ይፈቀድልሻል" አላት።
13አስቴርም፣ "ንጉሥን ደስ የሚያሰኘው
ከሆነ፣ በሱሳ የሚኖሩ አይሁድ የዛሬውን ዐዋጅ
ነገም እንዲደግሙት ፈቃድህ ይሁን፤ ዐሥሩ
የሐማ ወንዶች ልጆችም ዕንጨት ላይ ይሰ
ቀሉ" አለች።
14ንጉሡም ይህ እንዲሆን አዘዘ። በሱሳ ዐዋጅ
ተነገረ፤ ዐሥሩንም የሐማ ወንዶች ልጆች
ሰቀሏቸው። 15በሱሳ የሚኖሩ አይሁድ አዳር
በተባለው ወር በዐሥራ አራተኛው ቀን በአ
ንድነት መጡ፤ በሱሳም ሦስት መቶ ሰዎች
ገደሉ፤ በምርኮው ላይ ግን እጃቸውን አል
ዘረጉም።
16በዚህ ጊዜ በሌሎች በንጉሡ አውራጃ
ዎች የሚኖሩ የተቀሩት አይሁድ ራሳቸውን
ለመከላከልና ከጠላቶቻቸውም ለመገላገል
ተሰበሰቡ፤ ከሚጠሏቸውም ሰባ አምስት ሺህ
ገደሉ፤ በምርኮው ላይ ግን እጃቸውን አልዘ
ረጉም። 17ይህ የሆነው አዳር በተባለው
ወር ዐሥራ ሦስተኛ ቀን ነበር፤ በዐሥራ አራ
ተኛው ቀን ዐረፉ፤ ዕለቱንም የተድላና የደ
ስታ ቀን አድርገው ዋሉ።

### የፉሪም በዓል መከበር

18በሱሳ የሚኖሩ አይሁድ ግን በዐሥራ
ሦስተኛውና በዐሥራ አራተኛው ቀን ተሰብ
ስበው ነበር፤ ከዚያም በዐሥራ አምስተኛው
ቀን ዐረፉ፤ ዕለቱንም የተድላና የደስታ ቀን
አድርገው ዋሉ።
19በየመንደሩ የሚኖሩ የገጠር አይሁድ፣
የአዳርን ወር ዐሥራ አራተኛ ቀን የተድላና
የደስታ፣ እርስ በርሳቸውም ስጦታ የሚለዋ
ወጡበት ቀን አድርገው የሚያከብሩት ከዚሁ
የተነሣ ነው።
20መርዶክዮስ የተፈጸሙትን እነዚህን
ድርጊቶች ጻፈ፤ ደብዳቤ አዘጋጅቶም በመ
ላው የንጉሥ አርጤክስስ አውራጃ በቅርብና
በሩቅ ለሚገኙት አይሁድ ሁሉ ላከ፤ 21የላ
ከውም የአዳርን ወር ዐሥራ አራተኛና ዐሥራ
አምስተኛ ቀን በየዐመቱ እንዲያከብሩ ነው፤
22የሚያከብሩበትም ምክንያት አይሁድ ከጠ
ላቶቻቸው ዕረፍት ያገኙበት፣ ሐዘናቸው
ወደ ደስታ፣ ልቅሷቸውም ወደ ክብረ በዓል
የተለወጠበት ቀን ስለ ሆነ ነው። ቀኖቹንም
የተድላና የደስታ ቀኖች አድርገው፣ እርስ
በርሳቸውም የምግብ ስጦታ እየተለዋወጡና
ለድኾችም ስጦታ እየሰጡ እንዲያከብሩ
ጻፈላቸው።
23ስለዚህ አይሁድ መርዶክዮስ የጻፈላቸውን
ለመፈጸምና የጀመሩትን በዓል ለማክበር
ተስማሙ፤ 24ምክንያቱም የአይሁድ ሁሉ
ጠላት የሆነው የአጋጋዊው የሐመዳቱ ልጅ
ሐማ አይሁድን ለማጥፋት አሢሮ ነበር፤ ሊፈ
ጃቸውና ሊያጠፋቸውም ፉር የተባለ ዕጣ
ጥሎ ነበር። 25ሤራው በንጉሡ ዘንድ እንደ
ታወቀ[ሡ] ሐማ በአይሁድ ላይ የሸረበው ሤራ
በገዛ ራሱ ላይ እንዲጠመጠም፣ እርሱና
ወንዶች ልጆቹም በዕንጨት ላይ እንዲ
ሰቀሉ የጽሑፍ ትእዛዝ አስተላለፈ። 26ስለ
ዚህ እነዚህ ቀኖች ፉር ከሚለው ቃል
"ፉሪም" ለመባል በቁ። በዚህ ደብዳቤ ስለ

9፥4 ዘፀ11፥3፤ 2ሳሙ3፥1፤1ዜና11፥9፤ አስ8፥15
9፥5 ዘዳ25፥17-19፤ 1ሳሙ15፥3፤ዕዝ4፥6
9፥10 ዘፍ14፥23፤ 1ሳሙ14፥32፤15፥33፤ አስ3፥13፤5፥11፤መዝ 127፥3-5
9፥12 አስ5፥6፤7፥2
9፥13 ዘዳ21፥22-23፤አስ5፥11
9፥14 ዕዝ6፥14
9፥15 ዘፍ14፥23፤ አስ8፥11
9፥16 ዘዳ25፥19፤ 1ዜና4፥43፤አስ4፥14፤ 8፥11
9፥17 1ነገ3፥15
9፥19 አስ2፥9፤3፥7፤ ራእ11፥10
9፥22 2ነገ25፥30፤ ነህ8፥10፡12፤አስ4፥14፤ መዝ30፥11-12
9፥24 ዘፀ17፥8-16፤ ዘሌ16፥8፤አስ3፥6፡7
9፥25 ዘዳ21፥22-23፤ አስ7፥10፤መዝ7፥16
9፥26 አስ3፥7

[ሡ]25 ወይም፣ *አስቴር በንጉሡ ፊት በመጣች ጊዜ*

*9፥5-10፤* የአይሁድ ሕዝብ "የአማሌቃውያንን ስም ከምድር ገጽ የማጥፋቱን" ተግባር ከግብ ለማድረስ ተነሥተዋል (ዘፀ17፥16፤ ዘዳ25፥17-19፤ የ3፥1-6 ማብ ይመ)። በዚህ ክፍል የተጠቀሰው ሁኔታ ከ1ሳሙ15 ጋር ተቃራኒ ነው። ንጉሡ ምርኮ እንዲወስዱ ቢፈቅድላቸውም፣ ሕዝቡ ግን ምርኮ ከመውሰድ መቈጠቡን ጸሓፊው ደጋግሞ ገልጾአል (8፥11)። ከአምስት መቶ ዓመት በፊት፣ ንጉሥ ሳኦል ከአማሌቃውያን ጋር ጦርነት አድርጎ ምርኮ ስለ ወሰደ የንጉሥነት ሥልጣኑን አጥቶአል። (1ሳሙ 15፥17-19)፤ በዚህ ክፍል የሚታየው ምርኮ ለመውሰድ ያለመስ ገብገብ ግን፤ ለመርዶክዮስ የቤተ መንግሥት ሥልጣን አስገኝቶለታል (ቍ20-23)። ቍ15-16 ይመ፤ ከዘፍ 14፥22-24 ጋር ያነጻጽሩ።

9፥10 *የሐማ ... ወንዶች ልጆች፤* በ5፥11 ላይ ከተጠቀሰው በመቀጠል ለሁለተኛ ጊዜ በዚህ ክፍል ስለ ሐማ ልጆች ተጠቅሶ አል።

*9፥12፤* 5፥3፡6፤7፥2 ይመ።

*9፥13፤* እዚህ ላይ ሰዎችን መስቀል፣ የመግደያ መንገድ ሆኖ ሳይሆን፣ በድንን ሰቅሎ ለማሳየት ነው። (ቍ7-10 እና የ2፥23 ማብ ይመ)።

*9፥15-16፤* የቍ 5-10 ማብ ይመ።

9፥16፡22፤ *ከጠላቶቻቸውም ለመገላገል፤* ለእስራኤል እግዚአብሔር ከገባው የዕረፍት ቃል ኪዳን ጋር፣ አብሮ የሚሄድ ነው (ዘዳ 25፥19)። ሐማ ድል መመታቱ ለአይሁድ ሕዝብ ዕረፍትን አስገኝቶአል፤ ከ1ዜና 22፥6-10፤ መዝ 95፥8-11፤ ኢሳ 32፥18፤ ዕብ 3፥11-4፥11 ጋር ያነጻጽሩ።

*9፥18-19፤* ጸሓፊው ፉሪም የሚከበረው በሁለት የተለያዩ ቀናት እንደ ነበር ያመለክታል፤ በብዙ ከተሞች በአዳር ወር በዐሥራ አራተኛው ቀን ሲከበር፣ በሱሳ የነበሩ አይሁድ ግን በዐሥራ አምስተኛው ቀን ያከብሩት ነበር። በአሁኑ ዘመን በዐሥራ አራተኛው ቀን ያከብሩታል፤ በኢየሩሳሌም የሚከበረው ግን በዐሥራ አምስተኛው ቀን ነው።

9፥20 *መርዶክዮስ ... እነዚህን ድርጊቶች ጻፈ፤* አንዳንድ ሰዎች ከዚህ ተነሥተው መጽሐፈ አስቴርን የጻፈው መርዶክዮስ ራሱ ነው ይላሉ፤ የሚታመነው አመለካከት ግን፣ መርዶክዮስ በላካቸው ደብዳቤዎቹ ውስጥ በወቅቱ የተፈጸሙትን ድርጊቶች መዝግቦ ይዞ ነበር የሚለው ነው።

9፥22 *የምግብ ስጦታ፤* የ2፥9 ማብ ይመ፤ ከነህ 8፥10፡12 ጋር ያነጻጽሩ።

9፥24፡26 *ፉር፤* የ3፥7 ማብ ይመ።

ተጻፈው ሁሉ፣ ስላዩትና ስለ ደረሰባቸውም
ነገር ሁሉ፣ 27አይሁድ በታዘዘውና በተወሰ
ነው ጊዜ እነርሱና ዘሮቻቸው፣ እነርሱን
የተጠጓቸውም ሁሉ እነዚህን ሁለት ቀኖች
በየዓመቱ ባለማቋረጥ እንዲያከብሩ ሥርዐት
አድርገው ራሳቸው ወሰኑ። 28እነዚህም ቀኖች
በእያንዳንዱ ትውልድ፣ በእያንዳንዱ ቤተ
ሰብ፣ በእያንዳንዱ አውራጃና በእያንዳንዱ
ከተማ መታሰብና መከበር ይኖርባቸዋል፤
ይኸውም እነዚህ የፉሪም ቀኖች በአይሁድ
ዘንድ ሳይከበሩ እንዳይቀሩ፤ መታሰቢያቸውም
ከዘሮቻቸው መካከል እንዳይደመሰስ ነው።
29ስለዚህ የአቢካኢል ልጅ ንግሥት አስ
ቴር ከአይሁዳዊው ከመርዶክዮስ ጋር በመ
ሆን፣ ፉሪምን አስመልክተው ይህችን ሁለ
ተኛዪቱን ደብዳቤ ለማጽናት በሙሉ ሥል
ጣን ጻፉ። 30መርዶክዮስም የመልካም
ምኞት መግለጫና ማረጋገጫ የሆነውን
ደብዳቤ በአርጤክስስ ግዛት ውስጥ በሚገ
ኙት አንድ መቶ ሃያ ሰባት አውራጃዎች
ለሚኖሩት አይሁድ ሁሉ ላከ፤ 31የላከውም
አይሁዳዊው መርዶክዮስና ንግሥት አስቴር
ባወጁላቸውና እንደዚሁም የጾሙንና የሰቈ
ቃውን ጊዜ በሚመለከት ለራሳቸውና ለዘራ
ቸው ባጸኑት ውሳኔ መሠረት እነዚህ የፉ
ሪም ቀኖች በተወሰነላቸው ጊዜ እንዲከበሩ
ነው። 32የአስቴር ዐዋጅ ስለ ፉሪም የወጣ
ውን ሥርዐት አጸና፤ ይህም በመዝገብ
ተጻፈ።

### የመርዶክዮስ ታላቅነት

10 ንጉሥ አርጤክስስ እስከ ባሕር ዳርቻ
በሚዘልቀው ግዛቱ ሁሉ ላይ ግብር
ጣለ። 2የኀይሉና የብርታቱ ሥራ ሁሉ እን
ዲሁም ንጉሡ መርዶክዮስን ለዚህ የላቀ
ማዕረግ እንዴት እንዳደረሰው የሚናገረው
በሜዶንና በፋርስ የታሪክ መጽሐፍ የተጻፈ
አይደለምን? 3አይሁዳዊው መርዶክዮስ በማዕ
ረግ ከንጉሡ ከአርጤክስስ ቀጥሎ ሁለተኛ፣
ከአይሁድ መካከልም ቀዳሚውን ስፍራ የያዘ
ሰው ነበር፤ ለወገኖቹ መልካም በማድረጉና
ለአይሁድም ሁሉ ደኅንነት የቆመ በመሆኑ፣
በብዙዎቹ አይሁድ ወገኖቹ ዘንድ እጅግ
የተከበረ ነበር።

9፥29 አስ2፥15
9፥30 አስ1፥1
9፥31 አስ4፥1-3፡16
10፥1 መዝ72፥10፤
97፥1
10፥2 ዘፍ41፥44፤
አስ2፥23፤8፥15
10፥3 ዘፍ41፥40፡
43፤ነህ2፥10፤ኢር29፥
4-7፤ዳን5፥7፤6፥3

9፥27 *እነርሱን የተጠጓቸውም ሁሉ፤* አንዳንድ ሰዎች ይህ አባባል አይሁድ ከአሕዛብ ወገን ሰዎችን ወደ ሃይማኖታቸው ያስገቡበትን ጊዜ ስለሚያመለክት፣ መጽሐፈ አስቴር መቼ እንደ ተጻፈ ለመገመት የሚረዳ ነው ይላሉ፤ በይበልጥ ግን በ8፥17 ላይ የተጠቀሱትን ሰዎች የሚያመለክት ይመስላል።

9፥31 *የጾሙንና፤* የ4፥3፡16 ማብ ይመ። ለዚህ ጾም የተለየ ቀን አልተወሰነለትም። አይሁድ፣ ሐማ እነርሱን ለማጥፋት ምቹ ነው ብሎ ያሰበውን (3፥7፡13 ይመ) የአዳር ወር ዐሥራ ሦስተኛ ቀን የጾም ቀን አድርገውታል፤ ይህንንም ጾም "የአስቴር ጾም" ብለው ይጠሩታል፤ ይህ ቀን ከፉሪም ክብረ በዓል አስቀድሞ የሚውል ቀን ነበር። ከአዳር ዐሥራ ሦስት እስከ ዐሥራ አምስት ያሉት፣ የእነዚህ ሦስት የድል መታሰቢያ የበዓል ቀናት መከበር በሥነ ጽሑፋዊ አቀራረቡ ሲታይ፣ አስቴር ንጉሡ ፊት ቀርባ ደጅ ከመጥናቷ አስቀድሞ (4፥16) ሦስት ቀን ከጾመችበት ጊዜ ጋር ሊገናዘብና ሊመዛዘን የሚችል ነው።

*10፥1-2፤* ጸሓፊው ስለ ግብር መጣል መጥቀሱ እርሱ ያገኘው ሌላ የታሪክ ምንጭ መኖሩን ያመለክታል፤ አንባቢም ተጨማሪ መረጃ እንዲያገኝና እንዲያረጋግጥ ይመራል (የ2፥23 ማብ ይመ)።

*10፥3፤* መርዶክዮስ ባገኘው የጠቅላይ ሚኒስትርነት ማዕ ረግ፣ ከስምንት ዓመት በላይ እንዳልቈየበት ይገመታል፤ ምክንያቱም በ465 ዓ.ቅ.ክ በእርሱ ቦታ ሌላ ሰው ተሹሞ እንደ ነበር የዓለም ታሪክ ይናገራል።